# መግቢያ

"እጽሕፍ ለክሙ ወራዙት እስመ ሞእክምዎ ለእኩይ፤ ጕብዞች ሆይ፥ ክፉውን አሸንፋችኋልና እጽፍላችኋለሁ" (1ኛ ዮሐ. 2÷13)፡፡

- "ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ ጕብዞች ሆይ እጽፍላችኋለሁ" ሲል እግዚአብሔር ስለወጣቶች የሚገልጸው ሚልእክት ያለው መሆኑን እንረዳለን፡፡ እግዚአብሔር ወጣቶችን በተማለከተ እንደማነበረሰቡ "አሁን ደርሰዋልና ቢሮጡ ያሜልጣሉ፣ ቢመቱ ይጥላሉ" ብሎ በራሳቸው ብልሃት አይተዋቸወም፡፡ ዛሬ የወጣቶች ሕይወት ጥያቄ ወስጥ እየወደቀ መጥቷል፡፡ ሆኖም ልበ አምላክ ዳዊት "እጅግ ተጨንቄአለሁ፤ ምሕረቱ ብዙ ነወና በእግዚአብሔር እጅ እንወደቅ፤ በሰው እጅ ግን አልወደቅ" እንዳለው የጭንቅ ቀን ሳይመጣ፣ ጉብዝናችንን ሳንከስር፣ ደስ የማያሰኙ ዓመታት ሳይከቡን በእግዚአብሔር እጅ እንወደቅ፡፡ (2ኛ ሳሙ: 24÷14)፡፡
- ወጣትነት ብዙ ነገሮች የሚፈጠሩት የእድሜ ክፍል ነው፡፡ ሦስቱ የመንፈሳዊ ሕይወት ባላንጣዎች ማለትም ሥጋ፣ ሰይጣንና ዓለም ወጣትነታችንን ታጥቀው ይዋጉታል፡፡ ወጣትነት ከብርታት ጋር የተያያዘ ስለሆነ ለብዙ ነገሮች ማጠቀሚያ ይሆናል፡፡ ዳሩ ግን ከሁሉ በላይ በበረት ተወልዶ፣ የሕማም ሰው ሆኖ፣ በመከራ ተንገላቶ፣ መስቀል ላይ ሞቶ ቤዛ የሆነን መድኃኔዓለም ወጣትነታችንን ይፈልገዋል፡፡ ይህም ሲባል በዕድሜ የገፉ አዛወንቶችን "የብዙ ዓመታት የሕይወት ተሞክሮ አላቸወና ከማንም የተሻለ ያወቃሉ" ብሎ ለሽምግልናቸው እንደሚይተዋቸው ልብ ይሏል፡፡ ነገር ግን ያ ደምግባት፣ እንደዚያ ያለው ጉልበት፣ እንደዚያ ያለው እወቀት፣ እንደዚያ ያለው አፍ የሚያስከድን የጨዋታ ለዛ በእግዚአብሔር ፈቃድ ላይ ቢወድቅ ወጣትነት ልክ በውኃ ዳር እንደተተከለች፣ ፍሬዋም ያለማቋረጥ እንደሚሆን ዛፍ በሆነ ነበር፡፡
- ነገር ግን በዙሪያችን የምናያቸው ዘመናዊነትና ንቃት የወጣትነትን ሕይወት ሲፈታተኑት ይስተዋላል፡፡ "አራዳ" እየተባባሉ በነወር

የሚያራረዱና "ነፍሱ" እየተባባሉ በነፍስ የሚሸሻጡ፥ "እንትናዬ" በሚል ቁልምጫ እየተጠራሩ በተግባር የሚካዱ ወጣቶች መኖራቸው ሲታሰብ ከልብ ያሳዝናል፡፡ ተጣም ያደገና የጠነከረን ግንድ እንዳንቆርጠው እንሳሳለን፤ እንዳናቀናው ደግሞ ይሠብራል እኛም አቅም እናጣለን፡፡ ዛሬ የምናዝንበት የወጣትነት ሕይወትም ከአስተዳደግ ችግር የሚመነጩ ናቸው፡፡ ጥሩ እየበሉ ካደጉት ልጆች በላይ ጥሩ እያሰቡ ያደጉ ልጆች ለምድሪቱ መፍትሔ ናቸው፡፡ ጠቢቡ ሰሎሞን "ልጅን በሚሄድበት መንገድ ምራው፤ በሸመገለም ጊዜ ከእርሱ ፈቀቅ አይልም" እንዳለው ልጅነት መንፈሳዊ ትኩረትና እንክብካቤን የሚሻ መሠረት ነው፡፡ (ምሳ. 22÷6)፡፡በጥሩ መሠረት በልጅነት ላይ በሚገባ ካልተሠራ ቀጣዩ የወጣትነት ሕይወት ሥጋትና ፍርሃት ይሆናል፡፡

- ❖ ስለዚህ ወላጆች ልጆቻቸውን በሚልካም ክትትል በማሳደግ ከወጣትነት ክፉ ተጽእኖ መታደግ አለባቸው፡፡ በተለይ ደግሞ ካህናት ወጣቶች ልጆቻቸውን በአባትነታቸው የማስተማር፣ የመምከርና የመገሠጽ ኃላፊነት ተጥሎባቸዋል፡፡ ይህ አልፎ አልፎ የምናደርገው ሳይሆን ቋሚ ተግባራችን ነው፡፡ ልክ እንደ ሳሙኤል "ብላቴናውም ሳሙኤል እያደገ ሔደ" የሚባልላቸውን ወጣቶች በመካከላችን ለማየት ከምሬትና ከምኞት ያለፈ መንፈሳዊ ተግባር ይጠበቅብናል፡፡ እንግዲህ እኔም ይህን ሀሳብ ከግንዛቤ ወስጥ በማስገባት "ክርስቲያናዊ ሕይወት እና ኦርቶዶክሳዊ አስተምህሮ ለወጣቶች" የምትለውን አነስተኛ መጽሐፍ ላዘጋጀላችሁ፡፡ ቸሩ እግዚአብሔር ራሳችሁንም ሆነ ሌላውን የምትለወጡበት የሕይወት ንባብ ያደርግላችሁ ዘንድ እጸልያለሁ፡፡

**ብፁዕ አባታችን አቡነ ሳሙኤል**

**በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ**

**ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ**

**ኮሚሽን ሊቀጳጳስ**

አዲስ አበባ

2007 ዓ.ም

# ምዕራፍ አንድ

## ወጣትነትና ፈተናዎቹ

### የፈተናዎቹ ሁኔታና ምንጮች

ሀ. ፈተና በብዙ መንገድ ሊመጣ ይችላል፡፡ ከቅናትና ከምቀኝነት በማሳት በቤተሰብ፣ በጓደኛ፣ በሥራ ባልደረባ፣ በጉረቤት፣ በሥራ ቦታ፣ በትምህርት ተቋማት፣ በአምልኮ ሥፍራ፣ ወዘተ፤ ሰው በሰው ይፈተናል ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሰው እንደተፈተነ ሁሉ (ማር. 8÷11፣ ሉቃ. 10÷25፣ ዘፍ. 37÷24)

ለ. በወጣትነት ሕይወት ያለ ሰው ራሱን ለአንድ መልካም ነገር ያዘጋጀ መሆኑን ራሱን ሊፈትን ይገባዋል፡፡ በሃይማኖት ብትኖሩ ራሳችሁን መርምሩ ራሳችሁን ፈትኑ (2ቆ 13÷5) እንዲል፡፡

ሐ. አንዳንድ ጊዜ ወጣቱ ትውልድ እግዚአብሔርን ለመፈታተን ይሞክራል፡፡ በተለያየ መንገድ አታድርግ የተባለውን ትእዛዝ በመተላለፍ ያደርጋል፡፡ ነገር ግን እንዳይፈታተን ተጽፏል (ዘጸ. 17÷2፣ ዘዳ. 6÷16)

መ. ሰይጣን ወጣቶችንም ሆነ በአጠቃላይ ሰዎችን ይፈትናል፤ ስለዚህም "ፈታኝ" ተብሏል፡፡ ሆኖም አማኞች በእግዚአብሔር ኃይል ሊቃወሙትና ድል ሊያደርጉት ይችላሉ፡፡ የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፡፡ (ኤፌ. 6÷11፣ ማቴ. 4÷3)

ሠ. የሰው እምነቱ ይገለጥ ዘንድ በተለያየ ሁኔታ ይፈተናል በዚህም ምክንያት ወጣቶች ትዕግሥትን፣ ጽድቅን ይማራሉ፣ የእግዚአብሔርንም ፍቅር በይበልጥ ያስተውላሉ እግዚአብሔር ኢያመክር ለእኪት ወወእቱሰ ኢያመክር ወኢመነሂ፡፡ አላ አሐዱ አሐዱ ይትመከር በፍትወተ እንቲአሁ፡፡ ሆኖም እግዚአብሔር አምላክ ሰወን በክፉ አይፈትንም ፈተናም ራሱ ኃጢአት አይደለም፡፡ ነገር ግን ሰው ሲፈተንና በምኞቱም ሲወድቅ ኃጢአት ይሠራል፡፡ (ያዕ. 1÷13፣ ዘፍ. 22÷1)

## ፈተናና የፈታኞች ጠቀሜታ

ፈተና በብዙ መንገድ ሊመጣ ይችላል፡፡ ሰይጣን ሰዎችን ይፈትናል፡፡ ስለዚህም (ፈታኝ) ተብሏል፡፡ መከራን በማብዛት፣ የማይገባ ምኞት በመቀስቀስ፣ ሰዎችን በማጣላት፣ ስለ እግዚአብሔር አምላክነትና እውነት ጥርጥር ወይም ሐሰትን በመዝራት ሰዎችን ሊጥላቸው ይሞክራል፡፡ ሆኖም የእምነት ሰዎች በእግዚአብሔር ኃይል ለቋቋሙትና ሊቃወሙት ይችላሉ፡፡ ዘእንበለ ይዕርብ ፀሐይ አቀፎሩ መዓተክሙ ወኢተሀብዎ ፍኖተ ለሰይጣን በቀጣችሁ ላይ ፀሐይ አይግባ ለዲያብሎስም ፈንታ አትስጡት እግዚአብሔር አምላክ የፈተናወን መውጫ መንገድ ያዘጋጅላቸዋል፡፡ (ማቴ.4÷4፣ ኤፌ.4÷27)፡፡

ሰው ሆይ! ማንኛወም ፈተና መልካም ነገር ለማድረግ ጥሩ አጋጣሚ ነው፡፡ በመንፈሳዊ ዕድገት ጉዞ ላይ ሳለህ ፈተና ክፉ ነገር ለማድረግ አጋጣሚ እንደሚሆንብህ ሁሉ ትክክለኛወን ነገር ለማወቅና እና ለማድረግ ጥሩ አጋጣሚ መሆኑንም ብትረዳ ፈተናው እንቅፋት ከመሆን ይልቅ ሚማኛ ይሆንልሃል፡፡

ሰይጣን አንተን ለማስናከል የሚጠቀምበት ዋና መሣሪያ ፈተና ቢሆንም በዚያው አንጻር እግዚአብሔር አንተን ለማክበር ይፈልገዋል፡፡ ከኃጢአት ይልቅ መልካም ነገር ለማድረግ በምትመርጥበት ጊዜ ሁሉ ለፈተና የተዘጋጀህ መሆን ይኖርብሃል፡፡ ይህን ለሚዳት በመጀመሪያ የእግዚአብሔር ቃል መጽሐፍ ቅዱስን ለይተህ ማወቅ አለብህ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትክክለኛ የትዕግሥት ትምህርት የምታገኝበት መዝገብህ ነው፡፡ (ገላ. 5÷22)፡፡

እግዚአብሔር አምላክ ነገሮችን እኛ ባቀድነው መሠረት እንዲሄዱ በማድረግ ብቻ ሳይሆን የትርምስና ግራ የመጋባት ጊዜን በሕይወታችን እንዲመጣ በመፍቀድ በእርሱ መተማመንን ይሰጠናል፡፡ አንድ ሰው የፀሐይ መጥለቅ ትዕይንት በመመልከት ወይም በመዝናናት ደስ ሊለው ይችል ይሆናል፡፡ እውነተኛ ደስታንና ሰላምን ለመሙላት የምንችለው ግን እንድንጨነቅ ወይም እንድንፈራ በሚያደርጉን ሁኔታዎች ወስጥ ሆነን በእግዚአብሔር ለመታመን በመምረጥ ነው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ትዕግሥትን በሕይወታችን የምናዳብረው በሚፈትኑን ሁኔታዎች ወስጥ ሆነን ነው፡፡ "ሥራ አካልን እንደሚያጠነክር ሁሉ አስቸጋሪ ሁኔታዎችም አእምሮን ያጠነክራሉ" ከሚፈታቀር ይልቅ ማጠላላት፣ ከመደጋገፍ ደግሞ ማጠለፍ፣ ከመቻቻልም መነቃቀፍ በዝቶና ጎልቶ በሚታይባት በዚች ዓለም ወስጥ ቅድስናን፣ ፍቅርንና ትሕትናን ገንዘብ ለማድረግ ትግሉ ቀላል አይደለም፡፡

በመንፈሳዊ ሕይወት ወስጥ ሳለህ አንተን ክፉ በሚያደርጉ በተለያዩ መንገዶች ተፈትነህ የሚታወቅ ከሆንኸ ጥሩ ሰው ነኝ ለማለት አትችልም፡፡ ታማኝነትህን በሚፈትን አጋጣሚ ወስጥ ካላለፍክ ግን ታማኝ ነህ ልትባል ይገባሃል፡፡ ሀቀኝነት እምነት የሚጐደል ፈተናን በማሸነፍ ይገነባል፡፡ አንድ ፈተና ድል ባደረግህ ጊዜ እውነተኛ ነህ፡፡ ኦርቶዶክሳዊ ክርስቲያን የሆነ ሁሉ ከሰይጣን በላይ ኃይል እንዳለው ይታወቃል፡፡ ኦርቶዶክሳዊ ፈተናዎች ሁሉ ተመሳሳይ ሂደቶችን ሲከተሉ ይታያሉ፡፡ ስለዚህ "ያልተፈተነ ሕይወት ለኑሮ አይመችም"፡፡ ይኸውም የወጣቶችን ሕያወነት ማጠናከር መቻሉ ነው፡፡

ሀ. ውስጣዊ ወይም አፍአዊ ፍላጎት ምንድነው?

ኃጢአታዊ ፍላጎት ሊሆን ይችላል፤ የበቀል ወይም የበላይ መሆን ወይም ደግሞ ተገቢ የሆነ ፍላጎት፤ ለምሳሌ የሚቀር የሚከበር ሊሆን ይችላል፤ ተገቢ የሆነን ፍላጎት በተሳሳተ መንገድ እንድትፈጽም ሰይጣን ሃሳብ በሚያቀርብልህ ጊዜ ነው፡፡ በአቋራጭ መንገድ ላለመሄድ ሁል ጊዜ ተጠንቀቅ፡፡ አቋራጭ አካሄዶች ብዙ ጊዜ የሚጠበቁ አደገኛ ፈተናዎች የሚያመጡ ይሆናሉ፡፡ አቋራጭ መንገዱን ትተህ ብዙ ጊዜና ጉልበት በሚጠይቀው ቀጥተኛ መንገድ ሂድ፡፡ የእግዚአብሔር ቃል የሚነግረን ግን በውስጣችን የሚጀምር መሆኑን ነው፡፡ ውስጣዊ ፍላጎት ከሌለህ ፈተና ሁልጊዜ የሚጀምረው በውጭ ባለው ሁኔታዎች ሳይሆን በአእምሮ ውስጥ ጭምር ነው፡፡ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲሁ ብሏል "ከሰው ልብ ብቻ የሚወጣት ክፉ ሐሳብ፣ ምንዝር፣ ስርቆት፣ ሰውመግደል ፣ዝሙት ፣ መከገብገብ፣ ክፉ ሐሳብ ማታለል ፣መዳራት ፣ምቀኝነት፣ ስም ማጥፋት፣ ትዕቢት፣ ስንፍና ናቸው፡" እነዚህ ክፉ ነገሮች ሁሉ ከሰው ይወጣሉ ሰውን ያስከስሱታል (ማር.2÷1-23)፡፡ ቅዱስ ጴጥሮስንና ይሁዳን ማየት ይቻላል፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ክህደቱ ከፍርሃትና ከጭንቀት የተነሣ ነው፤ ኀሊና ከውስጥ ሳይሆን በድንገት ከውጭ ባሉ ሁኔታዎች ተጽዕኖ የተፈጠረ ነው፡፡ የይሁዳ ግን ከውስጥ ከኀሊና የመጣ ነው፡፡ ይሁዳ በውስጡ ፍቅረ ንዋይ (የገንዘብ ፍቅርን) ስለ ጸነሰ ኃጢአትን ሠራ፤ መምህሩንም ሸጠ፡ "በውስጣችሁከሚዋጉትምኞታችሁ አይደለምን?" እንዲል

ለ. ጥርጣሬን በመፍጠር፡ -

ጥርጣሬ፣ ሰይጣን እግዚአብሔር አምላክ ስለ ኃጢአት አግባብ አለመሆን የተናገረውን እንድንጠራጠር ሊያደርገን ይሞክራል፡፡ በእውነት ይህ ስህተት ነውን? በእርግጥ እግዚአብሔር ይህን አታድርግ ብሏልን? የሚል ጥርጣሬን ይፈጥራል፡፡ የእግዚአብሔር ቃል ግን እንዲህ በማለት

ያስጠነቅቀናል፡ - "ማንም ከሕያው እግዚአብሔር የሚያስኮበልል ኃጢአትና የማያምን ልብ እንዳይኖረው ተጠንቀቁ" (ዕብ.3÷12) ፡፡

ሐ. በማታለል፡ -

ሰይጣን እውነት ለመናገር ስለማይችል ሁል ጊዜ አታላይ በመሆኑ "የሐሰት አባት" ተብሏል፡፡ የሚነግርህ ነገር ሁሉ ሐሰት ወይም ለመተካት ሲል "አትሞትምእንደ እግዚአብሔር አዋቂ ትሆናለህ እያለ አዳምን ያሳተ" ምንም አይመጣብህም ማንም አያውቅብህም በማለት ወሽቱን ይደረድራል፡፡ ይሁን እንጂ ትንሽ ኃጢአት እንደ ጽንስ አንድ ቀን ቀስ በቀስ ራሱን ይገልጣል፡፡ (ዮሐ. 8÷44)፡፡

መ. ባለማታዘዝ፡ -

አእምሮህ ወስጥ ስታብላላው የቆየኸውን ኃጢአት በድርጊት ትገልጠዋለህ፡፡ እንደ አሳብ የተጀመረው ክፉ ሀሳብ የነገር ፀባይ ሆኖ በተግባር ይወለዳል፡፡ ሚልካም ሀሳብህንና ትኩረትህን ለያዘው ነገር ሁሉ ትሸነፋለህ፡፡ የሰይጣንን ወሽት ያዕቆብ እንዲህ በማለት ያሳስበናል፡፡ "ነገር ግን እያንዳንዱ የሚፈተነው በራሱ ክፉ ምኞት ሲያስብና ሲታለል ነው፡፡ ምኞት ከፀነሰች በኋላ ኃጢአትን ትወልዳለች ኃጢአትም ካደገች በኋላ ሞትን ትወልዳለች የተወደዳችሁ ወንድሞች ሆይ አትሳቱ" (ያዕ.1÷14-16) እንዳለ፡፡

# ክፍል አንድ

## የፈተና ማለፊያ መንገዶች

የፈተናን ማለፊያ መንገድ አወቆ በአግባቡ ተቋቁሞ ወደ ሕይወት ለመተርጎም የአመጣጥን ሁኔታ ሚረዳቱ ይጠቅማል፡፡ ፈተናን ታሸንፈው ዘንድ ልትከተላቸው የሚገቡ የተለያዩ መንገዶች አሉ፡፡ "ደካማ ይቅር አይልም፣ ይቅር ባይነት የጠንካሮች ማለያ ነው" እንደሚባለው አንዳንድ ወጣቶች የሚፈተኑበትን አሳቦች በማሸነፍ ለማለፍ ባለመቻላቸው የበደለኛነት ስሜት ይሰማቸዋል፡፡

ከሚተን "ያለፍኩ" አይደለሁም ይላሉ፡፡ ተስፋ ይቆርጣሉ፤ በሚተናቸው ያፍራሉ፡፡ ይህ በክርስትና ሕይወት አለመብሰልና ነገሮችን በትክክል አለሚዳት ነው፡፡ "ታላቁ ክብራችን ያለመውደቃችን ሳይሆን በወደቅን ቁጥር ማነሣታችን ላይ ነው"

በአንድ በኩል ፈተናን እንደ በጐ ነገር ልንቆጥረው እንችላለን፡፡ ክፉ ፈቃዱን በሚጸም ላይ ያሉ ሰዎችን የራሱ ስለሆኑ ሰይጣን አይፈትናቸውም፡፡ ፈተና የድካም ወይም የዓለማዊነት ምልክት ብቻ ሳይሆን ሰይጣንም የሚጠላህ የመሆኑ ምልክት ነው፡፡ ሰው በመሆናችንና በወደቀው ዓለም በመኖራችን የሚማጠብን የነገሮች ክፍልም ነው፡፡ በመሆኑም በፈተና አትደነቅ፣ አትደንግጥ፣ ወይም ተስፋ አትቁረጥ፡፡ ፈተና አይቀሬ መሆኑና ማሉ በማሉ ልታስወግደው የማትችል ሰው መሆንህን ተገንዘብ፡፡ የእግዚአብሔር ቃል "ለሰው ሁሉ ከሚሆነው በቀር ምንም ፈተና አልደረሰባችሁም፡፡" 1 ቆሮ. 10÷13) ይላል፡፡

ሚተን ኃጢኢት አይደለም፡፡ ፈተና ኃጢኢት የሚሆነው በተሸነፍክበት ጊዜ ብቻ ነው፡፡ ወፎች ከራስህ በላይ እንዳይበሩ ልትከለክላቸው አትችልም፡፡ ራስህ ላይ ጎጆአቸውን እንዳይሠሩ ለሙድረግ ግን ትችላለህ፡፡ ሰይጣን አሳቦችን እንዳያቀርብልህ ልትከለክለው አትችልም፡፡ የሚያቀርብልህን አሳብ እምቢ ልትለው ግን ትችላለህ፡፡ (ዕብ.4÷5)

ወደ እግዚአብሔር ይበልጥ በቀረብክ ማጠን ሰይጣንም ይበልጥ ለፈትንህ ይሞክራል፡፡ በእምነት የእግዚአብሔር ልጅ ስትሆን ሰይጣን እንደተደራጀ የወንጀለኞች ቡድን ሚሄ ሊያጠፋህ ልብህን ይከፋፍለዋል፤ ፍርሃትና ድንጋጤ ይለቅብሃል፡፡

አንዳንዴ በሚጸለይ ላይ እንዳለህ ሰይጣን አሳብህ ባልሆነ መንገድ ሊያሳፍርህ በማቅድ ያልተለመደ ክፉ አሳብ ወደ አእምሮህ ያመጣል፡፡ ስለዚህ በድርጊቱ አትደናገጥ፣ አትፈር፡፡

የምትፈተንበትን ሁኔታ ለይተህ ካወቅህ ንቁ ሁን፡፡ ከሌሎች ይልቅ ለፈተና ይበልጥ የሚያጋልጡ አንዳንድ ሁኔታዎች አሉ፡፡ አንዳንዶቹ ወዲያውኑ እንድትወድቅ ሲያደርጉህ ሌሎቹ ደግሞ ምንም አያስቸግሩህም፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች በተለይ በድካምህ የሚመጡ ስለሆኑ ለይተህ ልታውቃቸው ይገባል፡፡ ምክንያቱም የሚያሰናክልህ ምን መሆኑን ሰይጣን በትክክል ስለሚያውቅ ወደ ሁኔታዎቹ ሊወስዱህ ያለማቋረጥ ይተጋል፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ እንዲህ በማለት ያስጠነቅቀናል፡- "ራሳችሁን የምትገዙ ሁኑ ንቁም ጠላታችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሳ አንበሳ ወዲያና ወዲህ ይዞራል" መቼ እንደምትፈተን፣ በየትኛው ቀንና ሰዓት ፈተና እንደሚበዛብህ በየትኛው ቦታ ላይ እንደሆነ ማሰቡ ጥሩ ሊሆን ይችላል፡፡ በሆንም ግን ፈተናን ለማለፍ የእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ብቻ ሳይሆን የሚያስፈልግህ ፈተናን ለማለፍ ያለህ ጽኑ እምነትና ፈተናን ሊያሳልፍልህ የሚችለው የአምላክህ ርዳታም ጭምር ነው፡፡

እንዲህ ብለህ ራስህን ጠይቅ፡- "በጣም በተፈተንኩ ጊዜ አብረውኝ የነበሩ ሰዎች እነማን ናቸው? ጓደኞቼስ? የሥራ ባልደረቦቼስ? የማላውቃቸው ሰዎችስ? ወይስ ብቻዬን ነበርኩን? በል፡፡ ይህንንም አስብ፡፡ የእግዚአብሔር ቃል" የምትፈተነው በምትደክምበትና ብቻህን በምትሆንበት፣ በሚከለችህና በተከፋህ ጊዜ እንደሆነ፣ ጉዳት በደረሰብህ፣ በተቆጣህ፣ በተጨነቅህ ወይም አንዳች ታላቅ ነገር የተከናወነልህ እንደሆነ ወይም በሌላም ምክንያት በሆን ለማወቅ ሞክር፡፡ ምቹ ጊዜና ሁኔታ በሚገጥምህ ሰዓት የምትፈተንባቸውን የተለዩ ሁኔታዎች ለይተህ ማወቅ በተቻለህ መጠን ከሁኔታዎቹ ለመራቅ ልትዘጋጅ ይረዳሃል፡፡ ፈተና ይመጣል ብለን እንድንጠበቅና እንደ አመጣጡ ለመጋፈጥ እንድንዘጋጅ የእግዚአብሔር ቃል የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ በመደጋገም ይነግረናል፡፡ (ማቴ. 26÷41፣ ኤፌ. 6÷10-18፣ 1ተሰ. 5÷6 1ጴጥ. 1÷13፣ 5÷8)፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም፡- "ለዲያብሎስ ሥፍራ አትስጡት" (ኤፌ. 4÷28) ብሏል፡፡ በብልሃት ማቀድ ፈተናን ይቀንሳል፡፡ በመጽሐፈ ምሳሌ ውስጥ እንዲህ የተባለውን ምክር እንከተል፡- "የእግርህን

መንገድ አቅና አካሄድህም ሁሉ ይጽና" "የቅኖች ጐዳና ከክፋት መራቅ ነው፤ መንገዱን የሚጠብቅ ሕይወቱን ይጠብቃል" (ምሳ.16÷17)

# ክፍል ሁለት

## ፈተናን ለማለፍ ራስን መግዛት

እግዚአብሔር በማንኛውም ጊዜና ወቅት አስቸኳይ ጥሪ የመቀበያ ልዩ ማሽን አለው፡፡ ፈተናን ለመቋቋም ርዳታ ትጠይቀው ዘንድ ስለሚፈልግ እንዲህ ብሏል፡፡ "በመከራ ቀን ጥራኝ አድንሃለሁ አንተም ታከብረኛለህ" (መዝ. 50÷15)፤ ይህም ጸሎት አምላክህ ደራሽ እንደሆነ ይገልጽልሃል፡፡ እባክህ ድረስልኝ? አድነኝ? ርዳኝ? የሚለው ጸሎት ፈተና በድንገት ሲያጠቃህ ወደረዳትህ እና አምላክህ የምትማፀንበት የርዳታ ጥሪ ነው፡፡ እግዚአብሔር አምላክ የድረስልን ጩኸታችንን የሚሰማው ድካማችንን የሚረዳና የሚራራልን በመሆኑ ነው፡፡ "ነገር ግን እግዚአብሔር የሚወዳችሁ ልጆቹ እንደመሆናችሁ ማጠን እርሱን ምሰሉ" (1ዮሐ. 3÷1)፡፡

እግዚአብሔር ፈተናን እንድናሸንፍ ሊረዳን በመጠበቅ ላይ ከሆንን ፊታችንን ወደ እርሱ የማንመልሰው ለምንድነው? እውነቱን እንናገር፣ አንዳንድ ጊዜ ርዳታ አንሻም፤ ስህተት መሆኑን ብናውቅም በፈተና መሸነፍን እንፈልጋለን፡፡ ይህን የምናደርገው እግዚአብሔር ለእኛ ከሚያውቀው ይልቅ ራሳችን የሚሻለንን እናውቃለን ብለን ስለምናስብ ነው፡፡

ሌላው ምክንያት ደግሞ በተመሳሳይ ኃጢአት በተደጋጋሚ በመሸነፍ ላይ ስለምንገኝ የእግዚአብሔርን ርዳታ ለመጠየቅ እናፍራለን፡፡ እግዚአብሔር ግን ፍጹም አይታክትም፣ አይሰለችም፣ በተደጋጋሚ ወደ እርሱ በመቅረባችን ምክንያት ትዕግሥቱ አያልቅም፡፡ "እንግዲህ ወደጸጋው ዙፋን በእምነት እንቅረብ"፡፡ (ዕብ. 4÷16)፡፡

ፈተናዎች የበለጠ በሃይማኖት እንድንጸና እና እንድናምን ያደርጉናል፡፡ አንድ ዛፍ ነፋስ በነፈሰበት ቁጥር ሥሮቹ እየበረቱ እንደሚሄዱ ፈተናን

በተቋቋምክ ጊዜ ሁሉ ይበልጥ እውነተኛ ክርስቲያን ትሆናለህ እንጂ በምትሰናከልበት ጊዜ አስከፊ ፍጻሜ ላይ ደረስክ ማለት አይደለም፡፡ ያኔ ከማሸነፍ ወይም ተስፋ ከመቁረጥ ወደ እግዚአብሔር ተመልከት፤ ርዳታውን ጠብቅ ፤ የኋላ ሽልማትህን ተስፋ ማንግሥት ሰማያትን አስታውስ፡ "በፈተና የሚጸና ሰው የተባረከ ነው ምክንያቱም ፈተና ይቋቋም ዘንድ እግዚአብሔር ለሚወዱት የሰጠውን ተስፋ የሕይወትን አክሊል ያገኛል፡፡" (ያዕ 1÷12) ፈተናን ለማለፍ ከክ□ ምኞት ሽሽ በንፁሕ ልብ ጽድቅን፣ እምነትን፣ ፍቅርን እና ሰላምን ተከተል፡፡ (1ኛ ጢሞ 2÷2)

በሰዎች ሁሉ ላይ ከደረሰው የተለየ ፈተና አልደረሰባችሁም፤ እግዚአብሔር ታማኝ ነው ስለዚህ ከምትችሉት በላይ እንድትፈተኑ አይተዋችሁም ነገር ግን በምትፈተኑበት ጊዜ ፈተናውን መታገስ እንድትችሉ መውጫ መንገዱን ያዘጋጅላችኋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ፈተና ልትሸከመው ከምትችለው በላይ የከበደ መስሎ ይሰማህ ይሆናል፡፡ ይህ ከሰይጣን የሚመጣ ሐሰት ነው፡፡ እግዚአብሔር ፈተናን ትቋቋምበት ዘንድ ወስጥህ ካኖረው አቅም የበለጠ ፈተና እንዲደርስብህ እንደሚፈቅድ ቃል ገብቷል፡፡ ሰይጣን ሊፈትንህ ሲፈልግ እግዚአብሔር ደግሞ የሚያሸንፈው ማንኛውም ፈተና እንዲደርስብህ አይፈቅድም፡፡ "ንጹሕ ሰው ሆኖ መከራ የደረሰበት ቅን ሰው ሆኖም የተደመሰሰ አይተህ ታውቅ እንደሆነ እስቲ ወደ ኋላ መለስ ብለህ አስብ" (ኢዮ. 4÷7)፡፡

## ወስጣዊ ሀሳብን ማቅናት

ፈተናን ለማሸነፍ የክፉ አሳባችንን ትኩረት እንድንቀይር ተመከረናል፡፡ አንድን ክፉ ሀሳብ ከአእምሮ ለመከላከል በሞከርህ ቁጥር ይበልጥ ወደ ትወስታ ክፍልህ ታስገባዋለህ፡፡ ፈተናን ከሚያመጣብህ ስሜት ጋር በመዋጋት ልታሸንፈው አትችልም፡፡ አንድን ስሜት ይበልጥ በተዋጋኸው ቁጥር ይበልጥ እያደከመህ ይቆጣጠርሃል፡፡ ባሰብከው ጊዜ ሁሉ ታጠነክረዋለህ፡፡ ፈተና ሁል ጊዜ የሚጀምረው በሐሳብ ነው፡፡ ሐሳብን በመሟከ የሚመጣን ፈተና የማስገወጃ ፈጣኑ መንገድ ትኩረትህን ሌላ ነገር ላይ ማድረግ ነው፡፡ ሀሳቡን አትዋጋው የትኩረት

አቅጣጫህን ግን ወደ ሌላ ለወጥና በሌላኛው ነገር ላይ አነጣጥር፡፡ ይህ ፈተናን የማሸነፊያ የመጀመሪያ እርምጃ ነው፡፡ "ጭንቅላትህ ስብ ከሆነ በፀሐይ አትሂድ"

ሀሳብ ብርቱ ኃይል አለው፡፡ ለዚህ ማስረጃ በዙሪያችን ያለ ሰው ያበላሻቸውንና ያለማቸውን ነገሮች መመልከት በቂ ነው፡፡ ሰው የሚሆነው ያሰበውን ነው፡፡ "በልቡ እንዳያስብ እንዲሁ ነወና" እንዲል (ምሳ. 23÷7)፡፡ ውጫዊ ኑሮአችን የውስጣችን ትራፊ ነው፡፡ የሚታዩ ተግባሮቻችን የአስተሳሰባችን ውጤቶች ናቸው፡፡ ራሳችንን እንዳዘጋጀነው ነን፡፡ ብንፈልግ እንደ አሳማ በላደን ዓለምን ማስጨቅ እንችላለን፡፡ ብንፈልግ ደግሞ እንደ ማርቲን ሉተር ብዙዎችን ማስረፍ እንችላለን፡፡ እግዚአብሔር የሰጠን ነጻ ፈቃድ ለዚህ ሀሳባችን መሠረት ሆኗል፡፡ ታዲያ የአስተሳሰብ ኃይል በመንፈስ ቁጥጥር ሥር ካልዋለ የጥፋት ፎርሙላ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡ አጥብቀህ ልብህን ጠብቅ፣ የሕይወት መውጫ ከእርሱ ነወና እንዲል (ምሳ. 4÷23)፡፡

ልብ የተባለው ግዙፉ ተፈጥሮ ሳይሆን የሰው የሕይወቱ ማዕከል የሆነው አስተሳሰቡ ነው፡፡ ምንጩ ከደፈረሰ ወራጁ እንደሚጠራ ሁሉ ከአስተሳሰቡ የተበላሸም ከተግባሩ አይፀዳም፡፡ ልብ በደከማበት ነገር አካል ሳይሠራ እንደሚደክመው ሁሉ ልብ ደስ ባለው ነገርም ሥራ አይደክመውም፡፡ አስተሳሰባችን ቅዱስ ከሆነ መልካም ጌታ ሆኗል ማለት ነው፡፡ ቀሪዎቹ ያሉን ነገሮች ደግሞ መልካም ለሌዎች ይሆኑናል፡፡

ሀሳባችን ወደ አተኮርንበት ነገር መሳባችን ብዙ ጊዜ የሚሆን ነገር ነው፡፡ ስለ አንድ ነገር ይበልጥ ባሰብክ ቁጥር ያ ነገር ይበልጥ አጥብቆ ይይዝሃል፡፡ ከኃጢአት ጋር በምታደርገው ጦርነት መሸነፍም ሆነ ማሸነፍ የሚከናወነው አእምሮ ውስጥ ነው፡፡ ትኩረትህን የሳበው ነገር አንተንም ያሸንፍሃል፡፡ ለዚህ ነው ኢዮብ እንዲህ ያለው፡፡ (ኢዮብ 31÷1)፡፡ ነቢዩ

ዳዊትም "ከንቱ ነገር ከማየት ዓይኖቼን መልስ በራስህ መንገድ እንደገና ሕያው አድርገኝ" ብሏል መዝ 119÷37)፡፡

ፈተና የሚጀምረው ትኩረትህን በመሳብ ነው፡፡ ትኩረትህን የሚያገኝ ነገር ደግሞ ስሜቶችህን ያነሣሣቸዋል፡፡ ስሜቶችህ በተራቸው ስለሚቀሰቅሱት የተሰማህን ነገር ታደርገዋለህ፡፡ ይህን ለማድረግ አልፈልግም በሚለው አሳብ ላይ ባተኮርክ ቁጥር ጉልበቱን አጠናክሮ ወደ ሚቦ ይስብሃል፡፡ ፈተናን ከመዋጋት ይልቅ ችላ ማለቱ የበለጠ ውጤት አለው፡፡ የሀሳብህ ትኩረት ሌላ ነገር ላይ ከሆነ ፈተና በአንተ ላይ ጉልበት ያጣል፡፡ ስለዚህ ፈተና ስልክ በሚደውልልህ ጊዜ ከእርሱ ጋር አትከራከር፡፡ ወጣቶች ሆይ! የፈተናውን ስልክ በጾም በጸሎት ስልኩን ዝጋው፡፡ "ከፉ አስተሳሰብህን ቀይርና ራስህን ለመልካም ነገር አዘጋጅ፡፡"

ፈተናን ድል የሚድረግ ቁርጥ ሀሳብ ካለህ አእምሮህን በመቆጣጠር ከተለያዩ ቦታዎችና ከማናኛ ብዙኃን የምትወስዳቸውን ነገሮች መመርመር ትጀምራለህ፡፡ ከኖሩ ሰዎች ሁሉ የላቀ ጥበብ የነበረው ሰው እንዲህ በማለት አስጠንቅቋል፡፡ "አጥብቀህ ልብህን ጠበቅ የሕይወት ማገኛ በር ከእርሱ ነውና" (ምሳ. 4÷23)፡፡ የሚደረቡ ነገሮችን ሁሉ ወደ አእምሮህ አታግበስብስ፡፡ የምታስባቸውን ነገሮች በጥንቃቄ ምረጥ፡፡ "ለክርስቶስ ለመታዘዝ አእምሮን ሁሉ እንማርካለን" ይህ በሕይወታችን የምንለማመደው ቢሆንም በመንፈስ ቅዱስ ርዳታ የአስተሳሰብ አቅጣጫህን ለማለወጥ ትችላለህ፡፡ (2ኛ ቆሮ. 10÷5)፡፡ ሀሳብን በኑዛዜ ማካፈል ያለብህን ትግል በታማኝነት የምታካፍለው አንድ ሰው ያስፈልግሃል ያም የንስሓ አባትህ ቢሆን ይመረጣል፡፡ አልያም ምሥጢር የሚያባክን ጓደኛህ ሊሆን ይችላል፡፡ "ለሥራቸው መልካም ወጤት ስለሚያገኙ ከአንድ ሁለት መሆን ይሻላል አንዱ ቢወድቅ ባልንጀራው ደግፎ ያነሣዋል" (መክ. 4÷9-10)

ከሚያቋርጥ መጥፎ ስምምነት ማለትም ከሱስና ከተለያዩ ፈተናዎች ጋር በምታደርገው ወጊያ በማሸነፍ ላይ ከሆንክና መልካም የሚድረግ ፍላጉትህ አልሳካ

እያለህ በተደጋጋሚ የበደለኛነት ስሜት ወስጥ ገብተህ በራስህ ጥረት ከችግሩ ለመላቀቅ አትችልምና የሰዎችን ርዳታ ጠይቅ፡፡ አንዳንድ ፈተናዎችን ልታሸንፋቸው የምትችለው በሚጸልይልህ፣ በሚያበረታታህና በሚከታተልህ ንስሓ አባት ርዳታ ብቻ ነው፡፡ እግዚአብሔር ለእድገትህና ለነፃነትህ የሰጠው ቃልኪዳን ይጸናል፡፡ ይህንንም እግዚአብሔር እንዲህ በማለት ይገልጣል፡- "ስለዚህ ተናዘዙ ትፈወሱም ዘንድ አንዱ ለሌላው ይጸልይ" (ያዕ. 5÷16)፡፡ ብዙኀ ትረድእ ጸሎቱ ለጻድቅ ትክል ወታሰልጥ (የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች)፡፡

በተደጋጋሚ ከሚያሸንፍህ ፈተና ለመዳወስ በእርግጥ ትፈልጋለህ? ለዚህ የእግዚአብሔር መፍትሔ ግልጥ ነው፡፡ በወስጥህ ልታፍነው አትሞክር ለንስሓ አባትህ ተናዘዘው፣ አትሸሽገው፣ ግለጠው፣ ስሜትህን ማግለጥ የፈወስህ መጀመሪያ ይሆናል፡፡ ጉዳትህን መደበቅ ያባብሰዋል፡፡ ችግሮች በጨለማ በሚፈጠር እያደጉና እየገዘፉ ይሄዳሉ፡፡ ለእወነት ብርሃን ሲጋለጡ ግን ይኮማዝራሉ፡፡ ሕመምህ የምሥጢሮችህን ያህል ነው፡፡ ስለዚህ ጭምብልህን አወልቅና በነፃነት ተመላለስ፡፡ ምክንያቱ አምላክህ የልብና የኩላሊት ዳኛ መሆኑን ማንዘብ ይኖርብሃል፡፡ "እግዚአብሔር አምላክ ሰይጣንን አገልጋዬን ኢዮብን ልብ ብለህ አየኸውን? እርሱን የመሰለ ታማኝና ደግ ሰው በምድር ላይ አይገኝም፤ እርሱ ከክፋት ሁሉ ርቆ እኔን የሚፈራ ቅን ሰው ነው አለ" (ኢዮ. 1÷8)፡፡

ስህተታችንን እንድንደብቅ የሚያደርገን አንዱ ኩራት ነው፡፡ ሁሉን "በቁጥጥራችን ሥር" እንዳዋልን አድርገው ሰዎች እንዲያስቡን እንፈልጋለን፡፡ እወነቱ ግን ልትገልጠው የማትችል ነገር ከቁጥጥርህ ውጭ የሆነ መሆኑ ነው፡፡ ይህም በገንዘብ ረገድ ያለብህ ችግር፣ በትዳርህ፣ በልጆችህ ዘንድ በአንተ ድብቅ ልማዶችህ እና ሱሶችህን በመሳሰሉት ወስጥ ሊገኝ ይችላል፡፡ ችግሩን ራስህ የምትፈታው ቢሆን ኑሮ እስካሁን ትፈታው ነበር፡፡ ነገር ግን አትችልም፡፡ ምክንያቱም ቆራጥነትና ግላዊ ወሳኔዎች ብቻ በቂ አይደሉምና፡፡

አንዳንድ ችግሮችህ ሥር የሰደዱ ግዙፍ የሆኑ እና በራስህ ጥረት ብቻ መፍትሔ ልታገኝላቸው የማይቻልህ ናቸው፡፡ በማሆኑም የሚያበረታታህ፣ የሚረዳህ የሚጸልይልህ ንስሐ አባት ወይም መንፈሳዊ ቤተሰብ ያስፈልግሃል፡፡ አንተም ስትበረታ ለሌሎች ወገኖች ተመሳሳዩን ልታደረግላቸው ትችላለህ፡፡

አንድ ሰው መጥቶ "ይህን እስከ ዛሬ ለማንም አልነገርኩም" በማለት ምሥጢሩን ሲገልጥልህ ስለዚህ ሰው ደስ ይልሃል፡፡ ምክንያቱም እንዲህ የሚያደርጉ ሰዎች ታላቅ እፎይታና ነፃነት እንደሚሰማቸው ስለሚታወቅ ነው፡፡ ምሥጢራቸውን ለታመኑ ወዳጃቸው በገለጡ ጊዜ በክፉ ሀሳብ የታሠሩበት እግር ብረት ሲፈታና ለወደፊት ሕይወታቸው የተስፋ ጭላንጭል ሲጣከቱ ለወዳጆቻችን ይታያቸዋል፡፡ ለንስሐ አባቶቻችን ስንገልጥላቸውም ዕረፍት፣ አጋርነትና ብርታት ይሰማናል፡፡

<u>ወጣት!</u> አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ በአንተ ዘንድ ችግሮች ወይም ፈተናዎች እንዳሉ ይሰማናል፡፡ ግን የሌለ ለማስመሰል የምትጣከረው ለምንድንነው? ስለምንድን ነው ለመግለጽ የምትፈራው? ችግሩን ብቻህን አትፈታውም፡፡ እርግጥ ነው ደካማነትህን ለሌሎች ለመግለጥ ራስን ዝቅ ማድረግ ይጠይቃል፡፡ ራስን ዝቅ አለማድረግ ግን ከችግርህ እንዳትላቀቅ ያደርግሃል፡፡ "እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል ... ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አስገዙ" (ያዕ. 4÷6-7) በማለት እንዲህ ካለው ፈተና መላገል እንድንችል ይመከረናል፡፡ "ሲሰደቡት መልሶ አልተሳደበም መከራን ሲቀበል ጻድቅ ፈራጅ በሆነው አምላክ ተስፋ አደረገ እንጂ አልዛተም" (1ጴጥ. 2÷23)፡፡

## ክፍል ሦስት

## የፈተናን በጐ ገጽታ ማሰብ

በዓለም ስንኖር ችግሮች የማይጠፉ መሆኑን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነግሮናል፡፡ በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ ብሎ (ዮሐ.

16÷33)፡፡ በሽታ የማያጠቃው፣ መከራ የማይነካው ወይም ፍጹም ከችግር ነፃ በሆነ የሕይወት ጐዳና ሰተት ብሎ የሚጓዝ ሰው የለም፡፡ ምድራዊ / ዓላማ ሕይወት ችግሮች ሁል ጊዜ የሚፈራረቅባት ናት፡፡ አንደኛውን ችግር በተወጣኸው ቁጥር ሌላው ለመተካት ይጠብቃል፡፡ ሁሉም ችግሮች አንተን በማነደግ ጠቃሚ ናቸው፡፡ ችግሮች ያሉ ወይም የተለመዱ መሆናቸውን ቅዱስ ጴጥሮስ እንዲህ በማለት ያረጋግጥልናል፡- "እንደ እሳት የሚፈትን ብርቱ መከራ በመቀበላችሁ እንግዳ ነገር እንደደረሰባችሁ በመቁጠር አትደነቁ" (1ጴጥ. 4÷12)፡፡

እግዚአብሔር ወደ ራሱ ሲያቀርብህ በችግሮች ይፈትንሃል፡፡ "እግዚአብሔር ልባቸው ለተሰበረ ቅርብ ነው፡፡ መንፈሳቸው የተሰበረውንም ያድናቸዋል" እንዳለ፡፡ (መዝ. 3÷418)፡፡ በመከራ ጊዜ ነው እውነተኛ ማስመሰል የሌለበት ጸሎት በመጸለይ በጭንቅ ጊዜ እንደ ነገሩ የሆነ ያልተገባ ጸሎት የማያስጸልይ ድካም አይኖረንም፡፡ በጭንቅ ጊዜ የምትጸልዩበት ጉልበት ዘፍ ባልክ ጊዜም አምላክህን በማሰብ ካንተ ጋር እንዲኖር አድርግ፡፡

ከልዑል እግዚአብሔር የምንማረው ከሌላ መንገድ ይልቅ በመከራ ጊዜ ነው፡፡ እግዚአብሔር ዮሴፍን እሥር ቤት እንዳይገባ (ዘፍጥ.39÷20-22)፣ ዳንኤል አንበሶች ጉድጓድ ወስጥ እንዳይወጣ (ዳን.6÷16-23)፣ ኤርምያስ ጉድጓድ ወስጥ እንዳይጣል፣ ጳወሎስ ሦስት የመርከብ አደጋዎች እንዳይደርሱበት (2ቆሮ. 11÷25) እና ሠለስቱ ደቂቅ እቶነ እሳት ወስጥ እንዳይጣሉ ሊያደርግ ይችል ነበር፡፡ ግን አላደረገውም፡፡ እነዚያ ነገሮች እንዲሆኑ ፈቀደ፡፡ በመከራ ወስጥ ያለፉት ሰዎች ወደ እግዚአብሔር ይበልጥ የቀረቡት የእግዚአብሔርን ዳኝነት የበለጠ የተረዱት እንዲህ ባለው ፈተና በወደቁ ጊዜ ነው፡፡ ለመንፈሳወያን ሰዎች ችግሮች ወደ እግዚአብሔር እንድንመለከትና ከራሳችን ይልቅ ከእርሱ እንድንደገፍ ያስገድዱናል፡፡ ይህን ጠቀሜታ አስመልክቶ ቅዱስ ጳወሎስ እንዲህ በማለት ይመሰክራል፡- "በእርግጥ የሞት ፍርድ እንደተፈረደብን ይሰማን ነበር፤ ይህም የሆነው ሙታንን በሚያስነሣ በእግዚአብሔር እንድንታመን እንጂ በራሳችን እንዳንታመን ነው" (2ቆሮ. 1÷9)፡፡ ያለህ ብቸኛ አምላክ

እግዚአብሔር ብቻ ሆኖ እስካልታየህ ድረስ የሚያስፈልግህ እርሱ ብቻ መሆኑን በፍጹም ልታውቅ አትችልም (ዳን. 3፥1-26) ምክንያቱም ምንም ይሁን ምን ከችግሮችህ የትኛውም ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ አይደርስብህም፡፡ የእግዚአብሔር ፍጡር በሆነ ሰው ላይ የሚደርሰው ማንኛውም ነገር በእግዚአብሔር በኩል ያለፈ ስለሚሆን ሰይጣን እና ሌሎቹም ለክፉ ቢያደርጉት እንኳን እርሱ ለመልካም ይጠቀምበታል፡፡

እግዚአብሔር ማንኛውንም ነገር ስለሚቆጣጠር አደጋዎች እርሱ ለአንተ ባለው እቅዱ ወስጥ የሚከናወኑ ነገሮች ናቸው፡፡ በሕይወትህ የሚደርስብህ ነገር ሁሉ መንፈሳዊ ጠቀሜታ አለው፡፡ (ሮሜ.8፥28-29)፡፡ ይህም የሆነበትን ምክንያት "እግዚአብሔር ከሚወዱት እና እንደ ሃሣብም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጐ እንዲሠራ እንደሚደረግላቸው እናውቃለን፡፡" (ሮሜ.8፥28)፡፡ በወደቀ ዓለም ወስጥ ስንኖር ሁሉ ተስተካክሎ እንዲሰጠን አንጠብቅም፡፡ ሁሉም ነገር እግዚአብሔር ባቀደው መሠረት ፍጹም በሆነ መንገድ ይቀርብልናል፡፡ ስለዚህ ነው እንዲህ ብለን እንድንጸልይ የተነገረን፡- "አባታችን ሆይ በሰማይ የምትኖር ስምህ ይቀደስ መንግሥትህ ትምጣ ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁም በምድር ትሁን" ማቴ.6፥10፡፡

እግዚአብሔርን የሚወዱና የሚታዘዙለት "ነገር ሁሉ ለበጐ" ይሆንላቸዋል፡፡ "ነገር ሁሉ" ሲል በሕይወትህ የሚደርስብህን ማለትም ስሕተቶችህን እና የሚጥሙህን ጉዳቶች ሁሉ ማለት ነው፡፡ አሳልፎና ይቅር ብሎ በበጐ ይተካልናል ማለት ነው፡፡ እግዚአብሔር ክፉ ነገርን ሁሉ በመልካም ነገር ይለውጣልና ነው፡፡

ጥሩ ነገሮች ጥሩ ወጤት እንዳላቸው ሁሉ አንተን የሚጎትቱ መጥፎ ነገሮች፥ በትዕግሥት ካለፍካቸው ያለኃጢአት ካሳለፍካቸው ወጤታቸው ጥሩ ይሆንልሃል እያለህ ነው፡፡ ወጣት ሆይ! አንተስ ስንቱን በዚህ መልኩ አሳልፈሃል? ይህ ቃል በሕይወትህ ሁሉ በጎ ነገር ያጋጥማሃል ማለቱ ሳይሆን የሚያጋጥሙህ ነገሮችን ወደ በጐ ዓላማ ይለውጥሃልና ማለቱ ነው፡፡ ነገሮች

ብዙዎቹ ከፉዎችና መጥፎዎች ናቸው፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር እንዲህ ካሉት የከፉ ነገሮች ውስጥ በጎ ነገርን በማውጣቱ የታወቀ ነው፡፡ በግልጥ በታወቀው የኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ ሐረግ ውስጥ (ማቴ. 1÷1-16) አራት ሴቶች ተመዝግበዋል፡፡ እነርሱም ትዕማር፣ ረዓብ፣ ሩት እና ቤርሳቤህ ናቸው፡፡ ትዕማር የባሏን አባት አታላ ማንነቷን ሳታሳውቅ ከእርሱ ፀነሰች፡፡ ረዓብ ሴት አዳሪ ነበረች፣ ሩት ደግሞ አይሁዳዊ ወንድ በማግባት የይሁዳውያንን ሕግ ጣሰች፡፡ ቤርሳቤህ ከዳዊት ጋር አመነዘረች፤ ይህ ድርጊቷም የባሏን ማደል አስከተለ፡፡ እነዚህ መልካም ስም ያላቸው አልነበሩም፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ከከፉ ነገር በጎውን አወጣ በእነርሱ የዘር ሐረግ በኩል ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲወለድ ዓለም ከጥፋቱ፣ ከከፋት እንዲድን ሆነ፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ እግዚአብሔርን ለሚወዱ እና እንደ ሃሳቡም ለተጠሩት... ብሎ ሲናገር ይህ ተስፋ የእግዚአብሔር ልጆች ለሆኑ ክርስቲያኖች ብቻ ነው እንጂ ለማንኛውም ሰው አልተሰጠም፡፡ እግዚአብሔርንና የእግዚአብሔርን ነገር ሁሉ በመጻረር ለሚኖሩ በራሳቸው መንገድ ለሚሄዱ ነገር ሁሉ ለከፉ ይሆንባቸዋል፡፡

እግዚአብሔር ከሁሉ የሚሻልህን ነገር ያውቃል፤ የሚያስበውም በጎውን ነው፡፡ ኤርምያስን እንዲህ ብሎታል፡- "ለእናንተ ያለኝን ዕቅድ እኔ አውቃለሁ... ፍጻሜው ያማረ ተስፋ የሚሰጥ እናንተንም የሚጠቅም እንጂ የሚጎዳ አይደለም" (ኤር. 29÷11)፡፡ ዮሴፍን ለባርነት የሸጡት ወንድሞቹን፡- "እናንተ እኔን ለመጉዳት አድርጋችሁት ነበር እግዚአብሔር ግን... ለበጎ ነገር አዋለው" (ዘፍ.50÷20) ባላቸው ጊዜ ይህንን እውነት ተገንዝቦ ነበር፡፡ ሕዝቅያስም ለሞት የሚያበቃ ሕመም ባደረበት ጊዜ ተመሳሳይ ስሜት ነበር ያስተጋባው፡- "እነሆ በሥቃይ የተጨነቅሁት ለጥቅሜ ሆነ" (ኢሳ. 38÷17)፡፡ ከመከራ እንዲያወጣህ ወደ እግዚአብሔር ስትጮህ ምላሹ "አይሆንም" ከሆነ ይህንን አስታውስ፡- "አባቶቻችን መልካም መስሎ እንደታያቸው ለጥቂት ጊዜ ይቀጡን ነበር እግዚአብሔር ግን የቅድስናው ተካፋዮች እንድንሆን ለእኛ ጥቅም ይቀጣናል፡፡" (ዕብ.12÷10)፡፡

የጽናት ምሥጢሩ ሥቃይህ፤ ጊዜያዊ ዋጋህ ግን ዘለዓለማዊ መሆኑን ማስታወስ ነው፡፡ ሙሴ በሕይወቱ ችግሮች በበዛበት ጊዜ ጸንቷል፡፡ ምክንያቱም "ወደ ፊት የሚቀበለውን ብድራት ከሩቅ ተመልክቶአልና" (ዕብ.11÷26)፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ በተመሳሳይ ሁኔታ በፈተና በመጽናት እንዲህ ብሏል፡- "ቀላልና ጊዜአዊ የሆነው መከራችን ወደር የማይገኝለት ዘለዓለማዊ ክብር ያስገኝልናል" (2ቆሮ. 4÷1)፡፡

አንተም ለአጭር ጊዜ አስተሳሰብ አትሸነፍ፡፡ የሚጨረሻው ወጤት ላይ አተኩር፡- "ልጆች ከሆንን ዘንድ በእርግጥ የመከራው ተካፋዮች ብንሆን የእግዚአብሔር ወራሾች ነን" (ሮሜ 8÷17) ብሏልና፡፡

"ሳታቋርጡ ጸልዩ በማንኛውም ሁኔታ አመስግኑ የእግዚአብሔር ፈቃድ ለእናንተ ይህ ነውና እግዚአብሔር የነገረን" "በሁሉ እንድናመሰግን" ነው፡፡ በደስታም በመከራም እንድናመሰግነው ይፈልጋል፡፡ እግዚአብሔር ችግርህን ለዓላማው መፈጸሚያ የሚጠቀምበት በመሆኑ እንድታመሰግነው ይፈልጋል፡፡ (1ኛ ተሰ.5÷17)

"ምን ጊዜም በጌታ ደስ ይበላችሁ" (ፊልጵ.4÷4) "ስለ ስቃይህ ደስ ይበልህ" አላለም፡፡ እንዲህ ያለው ሁኔታ በስቃይ የሚካት በሽታ ነው፡፡ ደስ የሚልህ "በጌታ" ነው፡፡ ምንም ይሁን ምን በእግዚአብሔር ፍቅር በእርሱ ጥበቃና ቸርነት ደስ ይልሃል፡፡ ጌታም እንዲህ አለ፡- "እነሆ ወሮታችሁ በሰማይ ታላቅ ነውና በዚያን ቀን ደስ ይበላችሁ፤ ፈንድቁም" (ሉቃስ 6÷23)፡፡

"መከራ ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቁጠሩት፡፡ ምክንያቱም የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንደሚያስገኝ ታውቃላችሁ፡፡ ምንም የማይጎድላችሁ ፍጹማንና ምሉዓን እንድትሆኑ ትዕግሥት ሥራውን ይፈጽም" (ያዕ.1÷2-4) ፡፡

አምላኬ ሆይ

ስህተት ባለበት እውነት

ክርክር ባለበት ስምምነት

ተስፋ መቁረጥ ባለበት መጽናናት

ጥርጣሬ ባለበት እምነት

ጥል ባለበት ፍቅር

ኀዘን ባለበት ደስታ

በደል ባለበት ይቅርታ

ጨለማ ባለበት ብርሃን

እንዲገኝ አድርግ

"እንደ ሞገዝ ያለ ክፋት፣ እንደ ጥላቻ ያለ ሻርክ (ዓሣ ነባሪ)፣ እንደ ጅልነት ያለ እባብ፣ እንደ ስስት ያለ ጎርፍ የለም"

# ክፍል አራት

## አስቸጋሪ ወጣት

አስቸጋሪ ወጣትነት የሌሉበት ሶፍራ አለ ለማለት በእጅጉ ያስቸግራል፡፡ ብዙዎቹ በአንድ ማሣሪያ ቤት አብረው የሚኖሩ፣ በቤተ ክርስቲያን አብረውን የሚያመልኩ እና የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ ነገር ግን እነዚህ አስቸጋሪ ወጣቶች ተለይተው የሚታወቁበት የራሳቸው የሆነ የተለየ ክፉ ጠባይ አላቸው፡፡ ይኸውም ከቁጥጥር ያለፈ ቁጣ፣ ጎጂ የሆነ ምላስ፣ በቀላሉ የመከፋት እና የማዘን ጠባይ የሚታይባቸው፣ አሁን ስቀው እና ተጫውተው እንደሆነ ከልቡናቸው በሚፈልቀው ክፋት ምክንያት ወዲያው የሚያኮርፉ፣ ዛሬ ያማከሩትንና ያደነቁትን ሰው በቅጽበት የሚቀፉና የሚታቹ፣ አሁን በጣም የወደዱትን ትንሽ ቆይተው በእጅጉ የሚጠሉ፣ ስለ ራሳቸው እንጂ ስለ ሌላው ሰው ፍላጎት እና ፈቃድ በፍጹም ግድ የሌላቸው፣ ተጠራጣሪዎች፣ ስጉዎች፣ በየጥቃቅኑ ምክንያት የሚጫጩ ስግብግቦች፣ በዚህች ምድር እኛ ብቻ እንኑር የሚሉ ሆዳሞች፣ የሌላው ሰው ጉዳይ የሚይሰማቸውና የሚይቆረቁራቸው፣ የተማሩ የሚመስሉ አንዳች የሚያወቁ፣ በተተኪ ተወልድ ላይ ሬት የሚዘሩ ወዘተ ናቸው፡፡

አስቸጋሪ ከሆነባችሁ ወጣት ጋር ያላችሁን ግንኙነት ሰላማዊ ለማድረግ፣ በየጊዜው በመካከላችሁ የሚፈጠሩትን ግጭቶች በተለያየ መንገድ ለመፍታት የተቻላችሁን ሁሉ ሞክራችሁ አቅቷችሁ ይሆን? የራሳችሁን ፍላጎት ትታችሁ አስቸጋሪው ወይም ነገረኛው ወጣት የጠየቀውን ሁሉ "እሺ!" በማለት ሰላም ለመፍጠር ሳትሞክሩ እንዳልቀራችሁ እንገምታለን፤ "እሺ! አንተ እንዳልክ" በማለት የራሳችሁን ፈቃድ መሥዋዕት ብታደርጉም በመካከላችሁ ያለውን ግጭት ማቃለል እንዳልቻላችሁ ስትረዱ፤ "ሰላም ማምጣት የሚቻለው በደካማነት ሳይሆን በብርቱነት ነው" ብላችሁ በማመን ኮስተር ብላችሁ ጽኑ የሆነ አቋም ለማያዝ ሞክራችሁም፣ የምትፈልጉትን ዓይነት ውጤት ስላላስገኘላችሁ፣ አሁንም አልቻልኩም! አቃተኝ! ብላችሁ ተስፋ ቆርጣችሁ ይሆን? ሁኔታው የበለጠ እየከፋ ሲመጣባችሁ፣ ያ አስቸጋሪ የሆነባችሁ ሰው፣ የእናንተን ሕይወት መራራ በማድረግ እናንተን ለመቅጣት ታስቦ የተፈጠረ፣ እናንተ ደግሞ የእርሱን ሕይወት ለማጣፈጥ ብቻ እግዚአብሔር "የመሥዋዕት በግ" አድርጎ የፈጠራችሁ መስሎ ተሰምቷችሁ ያውቅ ይሆን? በቀመሳችሁትስ መራራ ሕይወት ምክንያት ከላይ የጠቀስነውን ዓይነት ስሜት ቢሰማችሁ፣ ከአስቸጋሪው ሰው በስተቀር የሚረድባችሁ ሌላ አካል ይኖራል ብላችሁ አትገምቱ ይሆናል፡፡ "አእምሮው ከጠጓ ቻ የተሳለ" እንደተባለ፡፡

## **አስቸጋሪ ወጣቶች እንዴት ዓይነቶች ናቸው?**

ተለይተው የሚታወቁበትስ ምልክታቸው ምንድነው? አስቸጋሪ ሰዎች ተለዋዋጭ ባሕሪ ስላላቸው ምን እንደሚወዱ እና ምን እንደሚጠሉ፣ ምን እንደሚያስደስታቸውና እንደሚያስደስታቸው ለይቶ ማወቅ በጣም አስቸጋሪ የሚሆንበት ጊዜ አለ፡፡ አስቸጋሪ ሰዎች እውነተኛ ማንነታቸው እንዳይታወቅባቸው በቀልጣፋ ንግግራቸው ራሳቸውን የመደበቅ ልዩ ችሎታ ያላቸው በመሆናቸው ቀረብ ብለው ካላዩአቸው በስተቀር ሰላማዊ ሰው በማምሰል ብዙዎችን "አስቸጋሪ" የምንላቸው ሰዎች በባሕሪያቸው እንዲሁም የአስቸጋሪነታቸው መጠን የተለያየ ይሁን እንጂ ሁሉም የሚመሳሰሉበት አንድ ነገር አለ፡፡ ይህም ከእነርሱ ጋር ተቀራርቦ መኖር፣ አብሮ መሥራትም ሆነ ቤተ ክርስቲያን አብሮ ማገልገል በጣም ከባድ መሆኑ

ነው፡፡ አስቸጋሪ ሰዎች ምን ዓይነት አስተሳሰብ እና ጠባይ እንዳላቸው ለማሳየት የሚከተሉትን ዘጠኝ ጠባዮች ከዚህ በታች እንመለከታለን፡፡

ሀ. <u>ተጠራጣሪነት</u>

አስቸጋሪ ወጣቶች ከሚታዩባቸው ጠባያት አንዱ በብዙ ነገር ተጠራጣሪ መሆናቸው ነው፡፡ በሃይማኖት፣ በሥልጣን፣ በሥራ፣ በማንኛውም ሚሊካም ግንኙነት ይጠራጠራሉ፡፡

ለ. <u>ቁጡነት</u>

አስቸጋሪ የወጣቶች ቁጣ በአግባቡ ወይም በሥርዓቱ

ሐ. <u>ነቃፊነት</u>

መንቀፍ ልማዳቸው የሆኑ ሰዎች ራሳቸውን ከሰው ሁሉ የበላይ አድርገው ሌላውን የበታች በማድረግ በየአደባባዩ በነቃፊ ቃል ንግግራቸውን ይከፍታሉ፡፡ እብሪት በተሞላበት ንግግራቸው አያወቁም እንዳይባሉ በማንኛውም ነገር ራሳቸውን ከፍ ከፍ በማድረግ የሚያሳዩትና የሚቀርቡት ሁሉን እንደሚያወቁ አድርገው ነው፡፡

መ. <u>ስለ ሌላ ሰው ስሜት ግድ የለሽነት</u>

አስቸጋሪ ሰዎች የሌላውን ሰው ስሜት ምን ያህል እንደሚጎዱ እያወቁ በግድ የለሽነት የመጣላቸውን ቃል ከአፋቸው አውጥተው ይወረወራሉ፡፡

ሠ. <u>አኩራፊነት</u>

ፊት ለፊት እንዲህ ዓይነት ቃላት ተናግረህ ለምን ትጎዳኛለኸ በማለት ፊንታ ማኩረፍ የሚቀናቸው ሰዎች አሉ፡፡ ባኮረፈኝ ቁጥር ሁል ጊዜ እርሱን ማሻማጡ አሁንስ ሰለቸኝ የምንል ስንቶች እንሆን? በዚሁ ምክንያት እናንተ በጸሎታችሁ ደግፉን የምንል ብዙዎች ነን፡፡ (2ቆሮ.1÷11)

ረ. <u>ለእኔ ብቻ ይደረግልኝ ባይነት</u>

ስለ ሌላ ሰው ግድ የሌላቸው ለራሳቸው ብቻ የሚያስቡ የዚህ ዓይነቱ ፀባያቸው ምክንያቱ ምን ይሆን? "ፈረሱ የታሰረበት ቦታ ማጥ ብቻ ነው፡" እንደተባለ፡፡

## ሰ. ተለዋዋጭነት

ተለዋዋጭ የሆነ ጠባይ ያላቸው ወጣቶች አሁን ጥሩ ሰው ማለውእንደሆነ ጥቂት ቆይተው መጥፎ ይሆናሉ፡፡ ለአንድ ሳምንት ያህል ሰላማዊ ሰው ማለው እንደሆነ ድንገት ባልታወቀ ምክንያት ፍጹም ተለወጠው ሌላ ሰው ይሆናሉ፡፡

## ሸ. አምባገነናዊነት

ሁልጊዜ ሌላውን በቁጥጥራቸው ሥር ለማዋል ስለሚሹ ከሰዎች ጋር ጥሩ የሆነ ግንኙነት መፍጠር አይችሉም፡፡ ሁሉን በእጃቸው ጭብጥ በእግራቸው እርግጥ ማድረግ ስለሚሹ የሌላውን ሐሳብ ምንም ያህል ጥሩና ትክክል ቢሆንም መቀበል አይፈልጉም፡፡ እያንዳንዳችሁ ሌሎችን የሚጠቅመውን እንጂ ራሳችሁን የሚጠቅመውን አትመልከቱ፡፡ (ፊል. 2÷4)፡፡

## ቀ. ተበቃይነት

በተበቃይነት አስቸጋሪ የሆኑ ወጣቶች በፀባያቸው ማንኛውም በጐ ነገር ጥሩ ሆኖ አይታያቸውም፡፡ ሌላውን ሰው ደስ የሚያሰኝ ነገር እነርሱን ደስ አያሰኛቸውም፡፡ የተለያዩ ምክንያቶችን በመፍጠር ከማብቀል ወደ ኋላ አይሉም፡፡ በእነርሱ ዘንድ ፈሪሃ እግዚአብሔርና ሃይማኖት ቦታ የለውም፡፡

ከእንዲህ ዓይነቱ እጅግ አስቸጋሪ ወጣት ጋር የሚኖር ወይም የሚሠራ ማንኛውም ሰው በቅድሚያ ማወቅ ያለበት፣ ከላይ የገለጽናቸውንና ሌሎችንም የአስቸጋሪነት ጠባይና እንዲሁም ከአስቸጋሪው ሰው ጋር አብሮ ሲኖር ሁልጊዜ ለጥቃት የተጋለጠ መሆኑን ነው፡፡ ይኸውም አስቸጋሪ ወጣቶችን ለማማከር ወይም የአስቸጋሪ ወጣቶችን ጠባይ ለማለወጥ ሳይሆን አስቸጋሪ ሰዎች ተለይተው የሚታወቁበትን ምልክቶች ለማጠቆምና እንዲሁም አብሮአቸው የሚኖረው ሰው፣ አስቸጋሪ ሰዎች ጠባይና ድርጊት እንዳይጎዳ ራሱን ማጠበቅ የሚችልባቸውን አንዳንድ መንገዶችን ለማጠቆም ነው፡፡ አስቸጋሪ የሆኑ ሰዎችንና ጎጂነት ያለውን ጠባያቸውን ለይተን እንድናውቅና እንዲሁም አብረን እንዴት መኖርና መሥራት እንደምንችል ጠቃሚ የሆነ ምክር ያስፈልገናል፡፡ ያለአግባብም ተስፋ እንዳንቆርጥ፣ በተረጋጋ መንፈስ መምራት እንድንችል፣ ዓላማችንን እንዳንስት፣

እግዚአብሔር የሰጠንን የማሪጥና የመወሰን ነጻነቱን እንዳንለቅ፣ እንዲሁም በአስቸጋሪ ሰዎች እንዳንነዳ አስፈላጊውን ድንበር ማበጀትና ድንበሩን እንዴት ማስጠበቅ እንደምንችል ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አለብን፡፡ ይህን ካደረግን ድንበር ምን እንደሆነ፣ እንዲሁም ድንበር የሌለው ሕይወት ምን ያህል ለጥቃት የተጋለጠ መሆኑን በቀላሉ ሚዳት እንችላለን፡፡ ሰው ከሰው ሁሉ ጋር ሁልጊዜ በሰላም አብሮ መኖር የሚቻል ቢሆን ኖሮ ጥሩ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ከልማዳችን እንደተረዳነው ከሰው ሁሉ ጋር ሁልጊዜ በሰላም መኖር አይቻልም፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "የሚቻላችሁ ቢሆን ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ለመኖር በእናንተ በኩል የሚያስፈልገውን ሁሉ አድርጉ" (ሮሜ 12÷18) ብሎ ባልጻፈም ነበር፡፡ እግዚአብሔር ለብቻችን እንድንኖር ስላልፈጠረን፣ ከሰው ሁሉ ጋር ያለን ግንኙነት አስቸጋሪ ሲሆንብን፣ ከሰው ሁሉ ሸሽተን ለብቻችን ለመኖር ከማሰብ ይልቅ ተቻችለን መኖር የምንችልበትን መንገድ ሚፈለግ አለብን፡፡

"ዓለም በሦስት ነገሮች ማለትም በፍትሕ፣ በእውነትና በሰላም ትጸናለች" እንዲሉ ቤት ያለ ምሰሶ ሰላምም ያለ ፍትሕ አይጸናም፡፡ በኅብረተሰብ ወስጥ ፍትሕ ካለ አንዱ የሌላውን ሀብት አይመኝከትም፡፡ የራሱን ትቶ በሌላው እጅ ያለውን በቅንዐት አያይም፤ ደግሞም ፍትሕና ሰላም በሰፈነበት ኅብረተሰብ ወስጥ አስቸጋሪ ሰዎች ብዙም አይኖሩም፡፡ ቢኖሩም እንኳ በሚፈጥሯቸው እኩይ ተግባራት በእጅጉ ስለሚታወቁ የሌላውን ሰላምና ሚልካም ሥራ ሲያናጉ ይለያሉ ሁሉም ከተገነዘባቸው ደግሞ ብዙም ሕይወት አይኖራቸውም፤ ከሩ ሥራቸውንም ሥር ሳይሰድ መቁረጥ ማየት ይቻላል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## ክርስቲያናዊ ጋብቻ ለወጣቶች

"ያገባ መልካም አደረገ፤ ያላገባም የተሻለ አደረገ፡፡" 1ቆሮ. 7÷38

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ይህን የጻፈው ለቆሮንቶስ ምእመናን ነው፡፡ ቆሮንቶስ የግሪክ ከተማ ናት፤ በአሚርኛ መጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት እንደተገለጠው ከአቴና 75 ኪ.ሜ. ያህል ትርቃለች፤ በሐዲስ ኪዳን ዘመን ስድስት መቶ ሺ ሰዎች የሚኖሩባት ትልቅ ከተማ ነበረች፣ አቀማመጥዋ በሁለቱ የግሪክ አወራጃዎች በመቄዶንያና በአካይያ መካከል በሚገኘው ልሳነ ምድር ላይ ነው፡፡ ከተሚቱ የተመሠረተችው በባሕር ማናኛ ላይ በመሆኑ ከምሥራቅና ከምዕራብ ለሚመጡ መርከቦች ምቹ ወደብ ነበረች፤ ከዚህም የተነሣ ንግድ እየተስፋፋበት ሄደ፤ ከተማይቱም እጅግ ሀብታም ሆነች፤ የከተማይቱ ነዋሪዎች የሚያመልኩት አፍሮዲቱ የምትባለውን የፍቅር አምላክ ነበረ፡፡ ቆሮንቶሳዊ ማባል የስድብ ስም እስከሚሆን ድረስ የዝሙት ኃጢአት በከተማይቱ በዛ፤ አብዛኞቹ ነዋሪዎች ግሪኮች ሲሆኑ ብዙ ሮማውያንም ይኖሩባት ነበር፤ አይሁድም ነበሩባት፡፡

የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ወንጌልን ለሰብክ ሁለተኛ ጊዜ ወጥቶ ሳለ ወደ ግሪክ ሀገር ሲደርስ ነው፡፡ (የሐዋ.15÷36፣ 16÷6-13)፡፡

ሐዋርያው ከአቴና ወደ ቆሮንቶስ አልፎ ከአንድ ዓመት ተከል በላይ እያስተማረ እዚያ ተቀማጠ (የሐዋ. 18÷1-18)፡፡

ቤተ ክርስቲያኒቱ ብታሳዝነውና ብታስቸግረው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ሁለት ጊዜ ሄዶ ምእመናንን የጠየቃቸው ይመስላል፡፡ (2ቆሮ. 13÷1)፡፡

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በቆሮንቶስ የክርስቲያንን ማኅበር አቋቁሞ ነበር (የሐዋ. 18÷1-18)፡፡ በኤፌሶን በነበረበት ጊዜ ከቆሮንቶስ ከመጡ እንግዶች የቤተ ክርስቲያኒቱን ሁኔታ ማለት ዝሙትና መጣት ይፈጸምባት እንደነበር ሰምቶአል፤ (1÷11፣ 11÷17፣ 5÷1፣ 6÷1)፡፡

ስለሆነም ሐዋርያው ስለእነዚህ ሁኔታዎች ምክሩን ለመስጠት መልእክቱን መጻፍ ጀመረ፡፡ መልእክቱ የተለያየ ርእስ አለው፤ ምዕራፍ 7 የተጻፈው በምእመናን ጥያቄ መሠረት ስለ ጋብቻ ነው፡፡ ሐዋርያው ስለ ጋብቻ ለተጠየቀው ሁለት መንገድ አሳይቷል ይኸውም የሚያገባ በድንግልና እንዲያገባ ማለት እስከ ጋብቻ ድረስ ሩካቤ ሥጋ ሳያደርግ ንጽሕናውን ጠብቆ እንዲቆይና ሁለቱም በድንግልና እንዲጋቡ አዟል፡፡ ጋብቻ የማይፈልግ ደግሞ በመታቀብ ድንግልናውን ጠብቆ እንዲኖር ፈቅዷል፡፡

ይህ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በምዕራፍ 7 ያስተማረው የማግባትና በድንግልና የመኖር ጉዳይ ሁለቱም ሕጉና ሥርዓቱ ከተጠበቀ በሕይወት ለመኖር የሚያስችልና ከእግዚአብሔር ጋር የሚያስማማ ነው፡፡ በተዐቅቦ ቆይቶ በድንግልና መጋባት ሕጋዊ ጋብቻ ነው፡፡ ርብቃ ለይስሐቅ በታጨች ጊዜ ድንግል ነበረች፤ (ዘፍ. 24÷16)፡፡

"ሰው ያልታጨችውን ድንግል ቢያስታት ከእርስዋም ጋር ቢተኛ ማጫዋን ሰጥቶ ሚስት ያድርጋት፤ አባትዋም እርስዋን እንዳይሰጠው ፈጽሞ እምቢ ቢል እንደ ደናግል ማጫ ያህል ብር ይክፈላት" (ዘጸ. 32÷16-17) ተብሎ በሙሴ ሕግ ተቀምጧል፡፡ አስገድዶ የደፈረ በእግዚአብሔርም ሕግ ሆነ በምድራዊ መንግሥት በሕግ ይቀጣል፡፡

በድንግልና መኖርም ከበሽታ ለመጠበቅ ከሚኖ ቻሉም በላይ በእግዚአብሔር መንግሥት ዋጋ እንደአለው የሚከተለው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ያስረዳናል፡፡

"ከሴቶች ጋር ያልረከሱ እነዚህ ናቸው፤ ደንግሎች ናቸውና በጉ ወደሚሄድበት የሚከተሉት እነዚህ ናቸው፡፡ ከእግዚአብሔርና ለበጉ በኩራት እንዲሆኑ ከሰዎች የተዋጁ እነዚህ ናቸው፤" (ራዕ. 14÷4)

በጋብቻ የሚኖሩ ሰዎች ግን ቅድመ ጋብቻ ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው፤ ጓደኛን ለመምረጥ በቅድሚያ ወደ እግዚአብሔር ጸሎት ማድረግ ያስፈልጋል፤ ሁሉም ነገር ያለ እግዚአብሔር ርዳታ አይሳካምና፤ ከዚያ ቀጥሎ የጓደኛን ሃይማኖትና ሥነ ምግባር በመከታተል ጥናት ማድረግ ነው፡፡ እጮኛሞች ለወደፊቱ ለመጋባታቸው ርግጠኞች ቢሆኑም ከጋብቻ በፊት ሩካቤ ሥጋ ሚፈጸም የለባቸውም፡፡

ጋብቻ ሁለት ተቃራኒ ያን ጾታዎችን አንድ አካል የሚያደርግ ምሥጢረ ቤተ ክርስቲያን ነው፡፡ መሠረታዊ ዓላማዎቹም -

ሀ. መባዛትና ዘር መተካት (ዘፍ. 1÷28)

ለ. መረዳዳት (ዘፍ. 2÷18፤ 20÷24)

ሐ. ከዝሙት መጠበቅ (1ቆሮ. 7÷2) ናቸው፡፡

ኦርቶዶክሳዊ ጋብቻን ከሌሎች የጋብቻ ዓይነቶች የሚለዩት መሠረታዊ ነገሮች እነዚህ ናቸው፡፡

ዛሬም ይህ ችግር በኅብረተሰቡ ሳይቀር በሰፊው ይታያል፡፡ ለዓለማዊ ሕግ ደግሞ ፍቺን ስለሚፈቅድ ብዙ ክርስቲያኖች ወደዚያው እየተሳቡ ጋብቻቸውን ከቤተ ክርስቲያን ውጭ ሲፈጽሙ ይገኛሉ፡፡ ከቤተ ክርስቲያን ውጭ ጋብቻቸውን የሚፈጽሙ ክርስቲያኖች ይበዛሉ፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ተጋቢዎች ፍችን በሚጠይቁበት ጊዜ እንዳይከለከሉ መሆኑ ታውቋል፡፡

በ6ቱ ቃላተ ወንጌል እንደተደነገገው እዚህም ላይ በድጋሚ እንደተጻፈው ፍቺን በተመለከተ ጌታ፡- "እኔ ግን እላችኋለሁ፣ ያለ ዝሙት ምክንያት ሚስቱን ፈትቶ ሌላይቱን የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል፣ የተፈታችውንም የሚያገባ ያመነዝራል" በማለት ለፈሪሳውያንና ለደቀ መዛሙርቱ በግልጽ አስታውቋቸዋል (ማቴ. 19÷9)፡፡

እንግዲህ እዚህ ላይ ማንዘብ ያለብን እንደ ወንጌሉ ቃል ለፍቺ ምክንያት የሚሆነው ዝሙት እንጂ ሌላ ነገር ሊሆን አይችልም፡፡ ይልቁንስ ተጋቢዎች ሁለት ሳይሆኑ እንደ አንድ አካል መቈጠራቸውና የገቡትም ቃል ኪዳን በምሥጢረ ተክሊል የታሰረና በቅዱስ ቊርባን የጸና በሚገንም የታተመ መሆኑን እያሰቡ ፍቅራቸው እስከ መቃብራቸው ደርሶ ከዚያም በኋላ ሁለቱም የመንግሥት ሰማያት ወራሾች መሆናቸውን አምነውና በክርስቶስ ቃል ጸንተው መኖር በምድርም በሰማይም ይጠቅማቸዋል፡፡ አለበለዚያ ጋብቻቸውን አፍርሰው በአመንዝራነት የሚኖሩ ከሆነ ሕገ እግዚአብሔርን ከማፍረሳቸውም በላይ የቤተሰብን ማጣትን ያስከትላል፡፡

ስለ ጋብቻ ሕግና ስለ ፍቺ አለሚፈቀድ የሰሙት የጌታ ደቀ መዛሙርት "የባልና የሚስት ሥርዓት እንደዚህ ከሆነ መጋባት አይጠቅምም" አሉት፡፡ እርሱ ግን "ይህ ነገር ለተሰጣቸው ነው እንጂ ለሁሉ አይደለም" በማለት አስረድቷቸዋል፡፡

እዚህ ላይ ሁለት ነገሮችን እንማራለን፡፡ መጀመሪያ ከጋብቻ ውጭ በልቅ መኖር የማይገባ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ንጽሕናን ጠብቆ፣ ከሴት ርቆ በብቸኝነት መኖር ወንድና ሴት ሆነው ለተፈጠሩት ሁሉ ጋብቻ የተፈቀደ አስፈላጊ እንደሆነ እንረዳለን፡፡ ሁለተኛው ነገር ደግሞ የሚያስገነዝበን ያለ ጋብቻ ሊኖሩ የሚገባቸውን ሰዎች የሚያመለክት ነው፡፡

ስለዚህ የጋብቻ ሥርዓት በሁሉም የታዘዘ ሕግ ነው፡፡ ለብቻ መኖር ግን ጌታ እንደአለው ለተሰጣቸው ነው እንጂ ለሁሉ አይደለም፡፡ አባቶች ይህን ሲያብራሩ "ይህ ንጽሕና ጠብቆ መኖር ለሁሉም አይቻልም፤ ሀብተ ንጽሕና ለተሰጠው አራቱ ባሕርያት ለተስማሙለት ነው እንጂ" በማለት ተርጒመውታል (ትርጓሜ ወንጌል ማቴ. 19÷11)፡፡

የጋብቻ ሥርዓት የማይመለከታቸውን ሰዎች በሦስት ከፍሎ ጌታችን አሳይቶናል፡፡

ሀ. በእናታቸው ማኅፀን ጃንደረቦች ሆነው የተወለዱ አሉ፡፡

ለ. ሰው የሰለባቸው ጃንደረቦች አሉ፡፡

ሐ. ስለ መንግሥተ ሰማያት ራሳቸውን የሰለቡ ጃንደረቦች አሉ፡፡

ሳያገቡ ሊኖሩ የተሰጣቸው ሰዎች ምን ዓይነት እንደሆኑና ራሳቸውንም እንዲሚያሟሉ ሁኔታውን ከአስቀመጠላቸው በኋላ "ሊቀበለው የሚችል ይቀበለው" በማለት ደቀ መዛሙርቱን አሳስቧቸዋል (ማቴ. 19÷12)፡፡

ከላይ እንደተገለጸው የመጀመሪያው ዓይነት ጃንደረባ በተፈጥሮ የሚመጣ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በተፈጥሮ ሳይሆን በሰው እጅ አደጋ ደርሶበት ጃንደረባ የሆነ ማለት ነው፡ ሦስተኛው ግን ለመንግሥተ እግዚአብሔር አገልግሎት ሲል ራሱን ጃንደረባ ያደረገ ነው፡ ይህም ማለት የራሱን አካል በራሱ እጅ ያጐድላል ማለት አይደለም፡፡ የእግዚአብሔርን ወንጌለ መንግሥት ለማስፋፋት የተወለደበትን አገር ትቶ ያላመኑትን ለማስመንና ለማጥመቅ በባዕድ አገር እየተዘዋወረ አሕዛብን ለማስተማር በትጋት ላይ ሆኖ ስለሚደክም አንዳንድ ሰዎች ለእንደዚህ ዓይነት አገልግሎት ሲሉ ወይም ለሌላ መንፈሳዊ ዓላማ ሥራ ሲሉ ወይም በሌላ ተመሳሳይ ነገር ሲሉ ራሳቸውን ለእግዚአብሔር ወንጌለ መንግሥት መሥዋዕት በማድረግ ከጋብቻ ተለይተው የሚኖሩ ናቸው፡፡

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ጋብቻ የሰጠው መመሪያ በሕግ፣ በሥርዓተ ተክሊልና በሥርዓተ ቁርባን እየተፈጸመ ሕገ ወንጌልን እየጠበቀ እንዲፈጸም ነው፡፡ በዚህ ጋብቻ ከቤተ ክርስቲያን በቀር ማንኛውም ቤተሰብ ሆነ ማኅበረሰብ፣ የቤተሰብ ዳኝነት ሊያይ፣ ሊያፋታም ሆነ ሊለያይ አልተፈቀደለትም፡፡ "እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ጋብቻ ሰው አይለይ" ብሎ አዟልና፡፡ (ማቴ. 19÷12)

ጋብቻ ከአዳምና ከሔዋን ታሪክ የተጀመረ መሆኑን በመጥቀስ ጌታ አንድ ወንድ በአንዲት ሴት አንዲት ሴት በአንድ ወንድ መጽናት እንደ አለባቸው በሕገ ወንጌል ደንግጎታል፡፡ ጌታችን አምላካችን የመጀመሪያ ተአምራቱን ያሳየው በቃና ዘገሊላ በሠርግ ቤት ነበር፡፡ ይህም የሚያስረዳን ኦርቶዶክሳዊ ክርስቲያንን

በዚህ የጋብቻ ሥርዓት እንዲመሠ መሆኑን ነው፡፡ ጥሩ ቤተሰብ ከሌለ ጥሩ ኅብረተሰብ አይኖርም፡፡ ለጥሩ ቤተሰብ ደግሞ መሠረቱ በአንድ ለአንዲት ጋብቻ መጽናት ነው፡፡ የጋብቻ መፍረስ የቤተሰብን ኑሮ ከችግር ወስጥ መጣሉ አይቀርም፡፡ ይህ ችግር ደግሞ በቤተሰብ ወስጥ ብቻ ተወስኖ ስለማይቀር በጎረቤትና በኅብረተሰቡ ሁሉ ይዛመታል፡፡ ስለዚህ ፍቺ በቅዱስ በወንጌል የተከለከለ ነው፡፡

በዘመኑ ብሉይ ሰዎች እንደ ፍላጎታቸው ከአንድ በላይ ሚስት ያገቡ ነበር፡፡ ከአገቡም በኋላ ያለበቂ ምክንያት ሊያሰናብቱ መብት ነበራቸው፡፡ ይህ ልማድ ሕገ ኦሪት ከተሰጠ በኋላም ቀጠለ፡፡ ስለዚህ ፈሪሳውያን ይህን ጉዳይ ስለሚያውቁ ጌታን ሲፈታተኑት እንዲህ ብለው ጠየቁት፡- "ሰው በሆነው ምክንያት ሁሉ ሚስቱን ሊፈታ ተፈቅዶለታልን?" አሉት፡፡ እርሱ ግን መልሶ እንዲህ አለ፡- "ፈጣሪ በመጀመሪያ ወንድና ሴት አደረጋቸው፤ ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፤ ከሚስቱም ጋር ይተባበራል፤ ሁለቱም አንድ አካል ይሆናሉ፤ የሚለውን ቃል አላነበባችሁምን? ስለዚህ አንድ አካል ናቸው እንጂ ወደፊት ሁለት አይደሉም፡፡ እግዚአብሔር ያጣመረውን እንግዲህ ሰው አይለየው" በማለት ጌታችን አንድ ለአንዲት ጋብቻን አጽንቷል፡፡ (ማቴ. 19÷3-6፣ ዘፍ. 1÷27፣ 2÷24)፡፡

ፈሪሳውያን ጥያቄያቸውን በመቀጠል "እንግዲያ ሙሴ የፍችዋን ጽሕፈት ሰጥተው እንዲፈቷት ስለምን አዘዘ?" አሉት፡፡ ጌታም "ሙሴስ ስለ ልባችሁ ክፋት ሚስቶቻችሁን ትፈቱ ዘንድ ፈቀደላችሁ፣ ከጥንት ግን እንዲህ አልነበረም" በማለት መለሰላቸዋል (ማቴ. 19÷7-8፣ ዘዳ. 24÷1)፡፡

እዚህ ላይ እንደምናየው ሙሴ ፍችን የፈቀደው ስለ አይሁድ የልብ ክፋትና ስለነበረው ማኅበራዊ ችግር እንጂ በመሠረቱ የጋብቻ ሕግ አንድ በአንዲት መሆንና ጸንቶ መኖር እንደ ነበረበት ነው፡፡

እንግዲህ ይህ ሦስተኛው እንደ መጀመሪያዎቹ ሁለት ዓይነት ጃንደረቦች የአካል ጉድለት ስለሌለው የፈቃደ ሥጋ ፈተና አይለየውም፡፡ ስለዚህ ኑሮው

በመንፈሳዊ ተጋድሎ የተመሠረተ ነው፡፡ ጾምና ጸሎትን፣ ስግደትንና ትምህርትን፣ ተባሕትዎንና ገዳማዊነትን መሄራያ በማድረግ የዕለት ከዕለት ሥራውን እያከናወነ፣ መከራውንም እየተቀበለ የሥጋን ፈቃድ ለማሸነፍ በማጡ መበላትንና ማጣጣትን እየተለማመደ በተዓቅቦና በተጋድሎ ፈተናውን በእግዚአብሔር ረድኤት ድል ማድረግ ይችላል፡፡ ይህ ዓይነቱ አኗኗር ደናግል መነኮሳትንና መነኮሳይያትን ይጨምከታል፡፡

ስለዚህ አሁን ሁለት ዓይነት ሚእክቶችን ለማንዘብ ችለናል፡፡

በመጀመሪያ ሰው ሁሉ በተቻለ ማጠን በጋብቻ ሥርዓት አንድ በአንዲት ጸንቶ እንዲኖር ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቱን ሥርዓት ገንዘብ ያደረገ ቤተሰብ ሁሉ ይባረካል፡፡ ከዚህ ዓይነት ጋብቻ የሚገኙ ልጆችም ለአገርም፣ ለወገንም የሚጠቅሙ ጥሩ ዜጎች ይሆናሉ፡፡

በሚልካም ጋብቻ የሚኖሩ፣ አንድ በአንዲት የሚጸኑ፣ በአመንዝራነት የሚጣለሱ ግን በራሳቸውና በወገን ላይ ያልተጠበቀ ችግርን የሚያመጡ፣ መቅሰፍትን የሚጋብዙ ስለሆነ ትምህርትና የምክር አገልግሎት ያስፈልጋቸዋል፡፡ ሁለተኛው ዐቢይ ሚእክት ሰዎች ከጋብቻም በፊት ተዐቅቦን (መታቀብን) ገንዘብ ማድረግ እንደ አለባቸው ሚዳትና ለሌሎች ማስረዳት ይገባል፡፡

ከጋብቻ በፊት የተባለው ብዙ ብቸኞችንና በተለይም በወጣትነት ዕድሜ ክልል ያሉትን ለዐቅመ አዳምና ለዐቅመ ሔዋን የደረሱትንና ያልደረሱትንም ልጆች ሁሉ ይጨምከታል፡፡

እነዚህን በዕድሜ በፆታ ለይቶ ማስተማርና መምከር ያስፈልጋል፤ ትምህርት በልጅነት ነውና፡፡ በቤተሰብና በሰንበት ት/ቤት አማካይነት ልጆች በክፉ በሽታና በጐጂ ልማዳዊ ባህል እንዳይጠመዱ በቅድሚያ መምከርና ማስጠንቀቅ ይገባል፡፡ እንደተባለው ለልጆችም ለአዋቂዎችም ከማጠጥና ከአደገኛ ዕፀዋት እንዲጠበቁ፣ አስገድዶ ከመድፈርም ሆነ ከመደፈር፣ ከመጥለፍም ሆነ ከማጠለፍ፣ ከሌላም አደጋ ሁሉ ላይ እንዳይወድቁ ያለ ዕድሜ ጋብቻና ያለአቻ ጋብቻም

እንዳይፈጽሙ የማስጠንቀቂያ ትምህርት በቅድሚያ ማስማት የቤተ ክርስቲያናችን ዐቢይ መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት ሆኖ መቈጠር አለበት፡፡

ስለዚህ ካህናት የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ሁሉ ለልጆቹና ለትልልቆቹ በክፍል ለይቶ እንደ ችሎታቸውና እንደ ዕድሜያቸው በመመደብ የሚያስከታቸውን ቃለ እግዚአብሔር እየማጡ ማስተማርና በጋብቻ ሥርዓት አንድ በአንዲት ጸንተው መኖር እንደአለባቸውና እስከዚያው ድረስ ግን ከዝሙትና ከአደገኛ ዕፀዋት እንዲርቁ ማለት ጫት ከመቃም፣ ሲጋራ ከማጤስ፣ በማጠጥ ቤት ከመልከስከስ፣ ሐሺሽ ከማጠቀም፣ እንዲታቀቡ ጥብቅ ማስጠንቀቂያና ዝርዝር የተዐቅቦ መመሪያ ማስጠት ያስፈልጋል፡፡ የአስተሳሰብና የጠባይ ለውጥ እስኪያሳዩ ድረስ ከሰበካ ጉባኤው ከወላጆችና ከባለሙያዎች ጋር በመሆን በእየጊዜው ምክር በማስጠት፣ ወጣቶችን በነፍስም በሥጋም እንዲጠቀሙ ማድረግ ነው፡፡ አለበለዚያ አዳጊዎች ወጣቶች ገደል ሲገቡ ዝም ብሎ በቸልተኝነት ወይም ጉዳዩ አያገባኝም ብሎ መመልከት አሰብአዊነት ስለሆነ ኅብረተሰቡ፣ በተለይም ካህናትና መምህራን፣ ወላጆች ሁሉ ልጆቻችን ለተለየዩ ፈተናዎች እንዳይጋለጡ በየጊዜው በማስተማርና በመምከር፣ በማስጠንቀቅና በመገሠጽ ከጎጂ ባህልና ከአደገኛ ዕፀዋት ሱሰኝነት ማጠበቅና መንከባከብ የዘወትር አገልግሎታችን ይሁን፡፡

# ክፍል አንድ

## የክርስቲያናዊ ጋብቻ ማለያዎች

1. **ቃልኪዳን መሆኑ**፡- በወጣትነት ሕይወት ያሉ ሰዎች ትዳራቸውን በክርስቲያናዊ ጋብቻ ሲመሠርቱ በሌላው ዓለም ካለው የሚለይበት አንዱ ቃልኪዳን ነው፡፡ ቃልኪዳን ስንል በሕግ ላይ ከሚመሠረተው ግንኙነት ይለያል፡፡ ኪዳን ለራስ መታመንን ሲያጐላ ሕግ ግን በሕጉ መገዛትን ያሳያልና፡፡ በቃል ኪዳን ወስጥ እውነተኛነት፣ መሉ ማስጠትና በመንፈስ የሆነ ትስስር ሲኖረው በሕግ ግዴታ ሥር የሆነው ግን በደንብና በማጠብበቅ፣ ሰጥቶ በመቀበልና በነገሮች ላይ ሚደገፍን ያጐላል፡፡

በቃልኪዳን የሆነው ጋብቻ ፍቅራችንና ፈቃደኝነታችንን ሲጠይቅ በሕግ የሆነው ትስስር ግን ግዴታና መብትን በማስጠበቅ ብርቱ ተግባር ላይ ይጠምዳናል፡፡

ቃልኪዳን ከማለጫዎች አንዱ በሁኔታ ላይ አለመመስረቱ ነው፡፡ በክርስቲያኖች መካከል ሊኖር የሚችለው ትዳር በከፋም በተሻለም ነገር ወስጥ ታምኖ ለማለፍ ኪዳኑን የጠበቀ ነው፡፡ "ብትታመሚ ብትከሺ፣ ብትቆጪ ብታሳዝኚኝ፣ ወብትሽ ቢረግፍ፣ ባላሰብኩት መንገድ ብትጓዢም" ልንከባከብሽ ቃል እገባለሁ፤ "ብትታመም ብትከሳ፣ ብትቆጣና ብታሳዝነኝ፣ ወብትህ ቢረግፍ፣ ብታረጅ፣ ባላሰብከው መንገድ ብትጓዝም" ልንከባከብህ ቃል እገባለሁ ብለው የሚኖሩት ኑሮ ነው፡፡ ታዲያ የነበረው እንዳልነበረ ሲሆን ኑሮን የሚያናወጥ ነገር ሲመጣ ለገቡት ኪዳን ታምኖ መገኘት፣ ትልቅነት ነው፡፡ ወጣቶች ሆይ! መንፈሳዊነታችሁንና ትዳራችሁን ቸል አትበሉ፣ ሁኔታውን እለፉ፣ ኪዳናችሁን አስታውሱ፡፡

2. **ዘላቂ ነው፡-** "ምድሪቱ ላይ ምንም ቋሚ ነገር የለም" የሚለው አስተሳሰብ ብዙ ትዳሮችንም እየፈተነ ነው፡፡ ያዝ ለቀቅ፣ ብቅ ጥልቅ፣ ሖድ መጣ የብዙ ፍቅር መርኅ ነው፡፡ ጋብቻ አላቂ ሳይሆን ዘላቂ ነው፡፡ የሰማንያ ባል፣ የሰማንያ ሚስት የዕድሜ ልክ አጋር ሚስት ነው፡፡ ነቢዩ ዳዊት "የዘመኖቻችንም ዕድሜ ሰባ ዓመት፣ ቢበረታም ሰማንያ ዓመት ነው" ብሎ እንደተናገረው እስከ ዕድሜ ፍጻሜ ወይም እስከ ሞት አብሮና ታምኖ መዝለቅን የሚያስረዳ ነው፡፡ (መዝ. 89÷10)፡፡ ዛሬ ለመፋታት የሚቻኮለው ዘመናዊው ጋብቻ ክርስቲያናዊ መሠረት ስለሌለው ነው፡፡ "መፋታትን እጠላለሁ" እንዳለው እስከ ሞት ለሚጸናው፣ በፍቺም ለሚደመድመው የክርስትና ትዳር ጨክኖ መታዘዝ ለዘመናችን ወጣቶች ያስፈልጋል፡፡

❖ **ወጣቶች ሆይ**! በትዳራችሁ መካከል ተደጋጋሚ የሆኑ ችግሮች አሉ? ለችግሮቻችሁ የምትወስዷቸው እርምጃዎች ምን ይመስላሉ? ጠረጴዛ ማዙሪ ላይ ተቀምጦ ከመፋጠጥ ያልቅ እጅ ለእጅ ተያይዛችሁ በጉዳዩ ላይ ለማውራት አስባችሁ ታውቃላችሁ? ወይስ በትዳራችሁ ላይ ተስፋ ቆርጣችኋል? እንግዲህ የያዛችሁት ትዳር ረጅም ጉዞውን እንዲዘልቅ፣ እያንዳንዱ ማለዳ አዲስ እንዲሆንላችሁ፣ በመካከላችሁ ያለው ፍቅር እንዲጠነክርላችሁ በይቅርታ መተጣጠበ፣ ትዕግስትን ማዳበር፣ ትከሻን ማከፋት፣ ችግሩ ላይ ሳይሆን መፍትሔው ላይ በቂ ጊዜ መውሰድ እንዳለባችሁ እመካራችኋለሁና ተግባራዊ ታደርጉት ዘንድ አደራ አልኳችሁ፡፡

3. **ታማኝ ነው፡-** ታማኝነት በዘላቂነት ወስጥ የሚከተት ነጥብ ሲሆን የፍቅር ግንኙነት ሕያውነቱን እንደ ጠበቀ ይቀጥል ዘንድና የሚያቋርጥ እደገት እንዲያሳይ ትልቁን ሚና ይጫወታል፡፡ ታማኝነት በሚስት ወይም በባል ላይ ሌላ ከመወሽም የዘለለ ትርጉምም አለው፡፡ የገቡትን ኪዳን ከማጠበቅ ጀምሮ በመካከል ያለውን መፈላለግና ስበት አጠንክሮ መቆየት ታማኝነት ነው፡፡ ከውጪ የምንጠብቃቸውን አደጋዎች ታምነን እየተከላከልን ወስጣችን ሊንሸራተት ይችላል፡፡ ታማኝነትን በሙሉ ገጽታው ለመመልከት በሞከርን ቁጥር ሙታዘዛችን ልክ እንደሆነ ይመጣል፡፡ እርስ በእርስ ቸል አለመባባል፣ ያላችሁን ፍቅር በትጋት መመጋገቢ… የታማኝነት ገጽታ ነው፡፡

ሆኖም ክርስቲያን የሆነው አይሁዳዊም ሆነ አረማዊ ከክርስትና በፊት ይከተለው የነበረውን የዘርና የፆታ ልዩነት ከክርስትና በኋላም በክርስቲያኑ ኅብረተሰብ መካከል ለመተግበር ስለማቸከር ይህ ተግባር በሐዋርያው ዘመን ከክርስትናው እምነት ሕግ ጋር አብሮ ሊሄድ የሚችል ሆኖ አልተገኘም፡፡ በክርስትና እምነት አንድ በሆነው ሕዝብ መካከልም መልካም ግንኙነትን የሚያሰፍን ሆኖ አልተገኘም፡፡ "አይሁዳዊ ወይም አረማዊ፣ ገዥ ወይም ተገዥ፣

ወንድ ወይም ሴት የለም፤ ሁላችሁም በኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ናችሁ" ሲል ይህን ወርቃማ ሚልእክት ያስተላለፈውም የዘመኑን ኅብረተሰብ ከዚህ የዘርና የፆታ ልዩነት ማኅፈስ ለማላቀቅ ነበር፡፡

በአሁኑ ጊዜ በተግባር ከሚታየውም ሆነ ከአለፈው ዘመን ታሪክ ሚረጋገጥ እንደሚቻለው የክርስትና እምነት በዘር፣ በፆታ፣ በቀለም በቋንቋ የተለያየውን የዓለም ኅብረተ ሰብእ አንድ ለማድረግ የቻለ የአንድነት ሃይማኖት ነው፡፡ በአንድ ክርስቲያናዊ ኅብረተ ሰብእ መካከል በእርግጥ የዕድሜ የማዕርግ፣ የትምህርት ደረጃ፣ የፆታ ልዩነት ሊኖር ይችላል፡፡ ሆኖም በቤተ ክርስቲያን የሚሰጠው አገልግሎት የፆታ ልዩነት ተከትሎ የሚፈጸም አይደለም፤ እምነትና አምልኮ ከእግዚአብሔር ዘንድ በሚሰጠው ጸጋም የዕድሜ የፆታ ልዩነት አይደረግም፡፡ "በእግዚአብሔር ዘንድ ወንድም ሴትም የለም" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የፆታ ልዩነት አለመኖሩን ሳይሆን በፆታ ልዩነት ምክንያት የሚፈጸም አድልዎ አለመኖሩን ነው፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም እንደ ክርስቲያናዊት ተቋምነቷ ይህን ትምህርት በተግባር ላይ ስታውል ኑራለች፤ በጥምቀት፣ በቁርባን፣ በሥርዓተ ጋብቻ በቡራኬ የፆታ ልዩነት አታደርግም፤ በእምነትና አምልኮ አፈጻጸም አንዱ ከአንዱ ሊበልጥ ይችላል፡፡ ይህ ማባለጥም በሁሉ ፆታ ሊታይ ይችላል፡፡ ከቅድስና ደረጃ መድረስ የሚቻለውም በእምነትና ምግባር ፍጹምነት ነው፡፡ ስለሆነም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን "ቅዱሳን" የሚባሉ ወንዶች እንዳሏት ሁሉ "ቅዱሳት" የሚባሉ ሴቶችም አሏት፡፡

"ሴት ለባልዋ ክብር ናት፤ ሴት ከወንድ ተገኝታለችና ሴት ከባልዋ አትለይ፤ ወንድም ከሚስቱ አይለይ፤ ሁላችሁም በጌታችን ኑሩ፤ ሴት ከወንድ እንደተገኘች እንዲሁ ወንድ ከሴት ተገኘ፤ ነገር ግን ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው፡፡" (1ቆሮ. 11÷2-16)

ሴት ለባልዋ ክብር እንደሆነች፣ ከጋብቻ በኋላ ሁለቱም አንድ ስለሆኑ ባል ከሚስቱ፣ ሚስትም ከባልዋ ማለየት እንደሚገባቸው፣ ሴት ከወንድ

እንደተገኘች እንዲሁም ወንድ ከሴት እንደተገኘና ይህ ሁሉ የሆነው ከእግዚአብሔር እንደሆነ በመግለጽ የወንድና ሴት ተፈጥሮንና የጋብቻን ምሥጢር ያስረዳል፡፡ "ሚስት ለባልዋ ክብር ናት" የሚለውን ቃል በሚያሳከት ቅዱስ መጽሐፍ ብዙ የሚለው አለ፡፡ ከዚያም ለዚህ ዝግጅት ማጠናከሪያ ሊረዳ የሚችለውን ለማዘከር ያህል ጠቢቡ ሰሎሞን "ደግ ሚስትን ያገኘ በረከትን አገኘ፤ ከእግዚአብሔርም ሞገስን ይቀበላል፤" ይላል (ምሳ. 18÷22)፡፡ በሌላ ምዕራፍም "ልባም ሴት ለባልዋ ዘውድ ናት" ይላል (ምሳ. 12÷4)፡፡ ከዚያም በመቀጠል "ቤትና ባለጸግነት ከአባቶች ዘንድ ይወረሳሉ፤ አስተዋይ ሚስት ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ ናት፤" (ምሳ. 19÷14)፡፡ ሚስት የእግዚአብሔር ስጦታ መሆንዋን አጉልቶ ይናገራል፡፡ ይህም በሚገባ ባልና ሚስት መካከል በተግባር እየታየ ስለሆነ ማብራሪያ የሚያስፈልገው አይሆንም፡፡

"ሴት ከባልዋ አትለይ፤ ወንድም ከሚስቱ አይለይ" የሚለውም ቃል በአንደኛ ዘይቤ ባልና ሚስት በፍች መለያየት የሌለባቸው መሆኑን የሚያመለክት በሆንም በሌላ ዘይቤ ግን በክብር ባል ከሚስቱ፣ ሚስትም ከባልዋ መለየት እንደሌለባት የሚያመለክት መሆኑን የቤተ ክርስቲያን መተርጉማን አመስጥረው ይናገራሉ፡፡

"ሁላችሁም በጌታ ኑሩ፤" የሚለው ቃል የሚያመለክተው "እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ሰው አይለይ፤" (ማቴ. 19÷6) ለሚለው አምሳካዊ ቃል ሁሉም ተገዥ ሆነው በቃልኪዳናቸው ጸንተው መኖር እንደአለባቸው የሚያበረታታ የምክር ቃል ነው፡፡ "ሴት ከወንድ እንደተገኘች እንዲሁም ወንድ ከሴት ተገኘ፤" የሚለውም ቃል ሔዋን ከአዳም እንደተገኘች ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ከእመቤታችን ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነሥቶ መወለዱን የሚያመለክት እንደሆነ በትርጓሜ ቤት ይታተታል፡፡

እንደሚታወቀው ጋብቻ ወንድና ሴት በቃል ኪዳን ተሳስረው እንዲኖሩ በማንኛውም ኅብረተ ሰብእ የተፈቀደና የተከበረ ሥርዓት ነው፡፡ ከጋብቻ በኋላ

ሁለቱ አንድ ሥጋ ይሆናሉ፤ ሥጋዊ ግንኙነታቸውም የአንድነታቸው ምልክት ነው፡፡ አዳም ብቻውን ይኖር ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃድ ስለአልሆነ ሔዋንን ከጎኑ በመፍጠር ረዳት ወይም የኑሮ ጓደኛ እንዲኖረው አድርጓል፡፡ ከዚያም ወዲህ ወንድ ያለ ሴት ሴትም ያለ ወንድ በብቸኝነት ይኖር ዘንድ የተፈጥሮ ሥርዓት በአለመሆኑ ጋብቻ ሊቋረጥ የማይችል ሥርዓት ሆኖ በሰው ልጅ ዓለም ላይ ሲፈጸም ኑሯል፤ ይኖራልም፡፡

"ባሎች እንደ ገዛ ራሳቸው አድርገው የገዛ ሚስቶቻቸውን ሊወዷቸው ይገባቸዋል፤ የገዛ ሚስቱን የሚወድ ራሱን ይወዳል፤ ማንም የገዛ ሥጋውን የሚጠላ ከቶ የለምና፡፡" (ኤፌ. 5÷28-30)

ሰው ከራስ ጠጉሩ እስከ እግር ጥፍሩ ያሉትን የአካል ክፍሎች በእኩልነት ይወዳቸዋል፤ ከአካሉ ክፍሎች ወስጥ አንዱን የሚወድ ሌላውን የሚጠላ የለም፡፡ ለወንድ ሚስቱም አካሉ ናትና ከአካላቱ አንዱን እንኳ እንደማይጠላ እሷንም እንደገዛ ሥጋው ይወደዳት አለ፡፡ የባልና ሚስት ፍቅር እንደ ክርስቶስና ቤተ ክርስቲያን (ምእመን) ፍቅር መሆኑን ቀደም ብሎ በቁጥር 25 ላይ ይኸው ሐዋርያ ገልጾታል፤ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን (ምእመንን) መውደዱን በተግባር አሳይቷል፡፡ ስለእርስዋ ራሱን ለሕማም ለሞት አሳልፎ ሰጥቷል፡፡ ደሙን በማፍሰሱ ቀድሷታል፤ በጥምቀተ ማይ አንጽቷታል፣ አክብሯታል (ማቴ. 4÷7) ባልም ሚስቱን መውደዱን በተግባር ማሳየት አለበት፤ እንደ ሐዋርያው ትእዛዝ ወጥቶ ወርዶ፣ ነግዶ አትርፎ፣ ወይም አርሶ ቆፍሮ ዘርቶ አምርቶ፣ ልብሷን አልብሶ ጉረሮዋን አስጊጦ ደስ አሰኝቶ ተንከባክቦ መያዝ አለበት፡፡ በሚስት ላይ ሚስት በማስቀመጥ የሕግ ሚስቱን ማስቀናት የለበትም፤ በላይዋ ላይ ዝሙት እየፈጸመ ሀብቷን ማባከን የለበትም፤ ገንዘብም ከእሱዋ እየደበቀ ለግል ፍላጎቱ ማዋል የለበትም፡፡ ይኸው ሐዋርያ በዚሁ ቃል "ባሎች ሆይ! ሚስቶቻችሁን ወደዱ፤ መራራም አትሁኑባቸው" ብሎ ለቆላስይስ ሰዎች ጽፏል፡፡ (ቆላ. 3÷19)

ዛሬ ወንዶች እንደ ቅዱስ ጳወሎስ ቃል ይሄዳሉ ወይ? ሚስቶቻቸውን ይወዳሉ ወይ? ብለን ብንጠይቅ ሙሉ አወንታዊ ሚልስ ማግኘት ያስቸግር ይሆናል፤ አንዳንድ ወንዶች ሚስቶቻቸውን ይደበድባሉ፡፡

ሴቶች በሀገራችን በሥራው ዘርፍ የሚያበረክቱት ድርሻ ከፍተኛ ነው፤ በተለይ በገጠሩ ያሉት ሴቶች በቀን ከ13-17 ሰዓት በአማካይ ይሠራሉ ተብሎ ይገመታል፡፡ ሆኖም ለሥራቸው ተገቢው ዋጋ ሲሰጠው አይታይም፡፡

ሴቶች በከተማም ሆነ በገጠር በአብዛኛው ለሚሰሙበት ሥራ ትንሽ ክፍያ ያለው እጅግ አድካሚ በጤናቸውም ላይ ጫና የሚፈጥር ነው፡፡

ሴትና ወንድ በኅብረተሰቡ ወስጥ የሚኖራቸው ሚና የሚለካው አንድ አገር ወስጥ በሚገኘው ሚናቸውም የሥራ ዕድል፣ ትምህርት፣ የጤና አገልግሎት በሆኑት ዘርፎች እንዲሁም እንደ ዜጋ በሚኖላከታቸው ሁሉ ከወንድ ጋር ሚዛናዊ በሆነ መንገድ በሚያደርጉት የተሳትፎ መጠን ነው፡፡

"እናንተ ባሎች ሆይ! ከሚስቶቻችሁ ጋር በማስተዋል አብራችሁ ኑሩ፤ ጸሎታችሁ እንዳይከለከል፣ አብረው ደግሞ የሕይወትን ጸጋ እንደሚወርሱ አድርጋችሁ አክብሩዋቸው፡፡" (1ጴጥ. 3÷7)

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ "እናንተ ወንዶች ከሚስቶቻችሁ ጋር ስትኖሩ ሚስቶቻችሁን አክብሩ አለ፡- አትናቁ፣ አታቃሉ ማለቱ ነው፡፡ ብንይዝ እናስቀራቸዋለን፤ ብናስር እናጠቢቃቸዋለን፤ ብንሮጥ እንቀድማቸዋለን ብላችሁ አትናቁ አታቃሉ ማለቱ ነው፡፡ ሚስቶቻችሁን ወጥታችሁ ወርዳችሁ ርዱ፤ ሀብታቸውን አታባክኑባቸው፤ ወደ አመንዝራ ሴት በመሄድና የግብረ ሥጋ ግንኙነት በመፈጸም በሽታ አታምጡባቸው፤ እነሱ ከእናንተ ጋር ክብርን ሕይወትን ይወርሳሉና አትናቋቸው፤ ጸሎታችሁ እንዳይከለከል ያለው የተጣሉ እንደሆነ እሷ ከጠበቃ፣ ከዳኛ፤ እሱ ከዋስ፣ ከዳኛ ሲሉ የጸሎት ጊዜ ያልፍባቸዋልና፤ ሁለተኛው በቂም በቀል ሆኖ የጸለዩት ጸሎት አያርግምና፤ ሦስተኛም ጸሎተ ተክለሊቸው እንዳትፈርስ ነው፡፡ ሲጋቡ አንድ ልብስ ለብሰው፣ አንድ ቀለበት አድርገው፣

ጸሎተ ተክለል ደርሶላቸው፣ አክሊል ደፍተው ይጋባሉ፡፡ የተጣሉ እንደሆነ ጸሎተ ተክሊላቸው እንዳይፈርስ ነው፡፡ ይህን በተመለከተ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በማንፈስ ብንኖር በመንፈስ ደግሞ እንመላለስ፤ እርስ በእርሳችሁ እየተነሣሣንና እየተቀናናን በከንቱ አንመካ ይላል ሐዋርያው፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ምክሩን ሲደመድም "የዚህ ሁሉ ፍጻሜ ግን እንደ አንድ ልብ መካሪ፣ አንድ ቃል ተናጋሪ ሆኖ መኖር ነው" አለ፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "እርስ በእርሳችሁ በአንድ አሳብ ተስማሙ፡ የትዕቢትን ነገር አታስቡ፣ ነገር ግን የትሕትናን ነገር ለማሠራት ትጉ፣ ልባሞችም የሆናችሁ አይምሰላችሁ" ብሎአል፡፡ (ሮሜ 12÷16)

# ምዕራፍ ሦስት

## የተባረኩ ወጣቶች

"ትውልደ ጻድቃን ይትባረኩ፤ የጻድቃን ልጆች ይባረካሉ፡፡" (መዝ. 111÷1-3)

"ጻድቃን" የሚባሉት ምን ዓይነት ሰዎች ናቸው?

ጻድቃን የሚባሉት እግዚአብሔርን የሚፈሩ፣ ትእዛዙንም የሚጠብቁ ሰውን የሚያከብሩ ሰዎች ናቸው፡፡ ነቢዩ ዳዊት፡- "እግዚአብሔርን የሚፈራ፣ ትእዛዙንም የሚጠብቅ ሰው ብፁዕ ነው፤" ይላል (መዝ. 111÷1)፡፡ የጻድቅ ሰው ልጁ፣ የልጅ ልጁ በዚህ ዓለም ክብሮ፣ ገንኖ ይኖራል፤ የጻድቃን ልጆች ይባረካሉ፤ ክብረ ሥጋ ክብረ ነፍስ፣ ብዕለ ሥጋ ብዕለ ነፍስ በቤቱ ሚስት በወገኖቹ ይኖራል፤ ጻድቁም ለዘለዓለም ይኖራል፡፡

አዎ፣ እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ወልዶ ይስማል፤ ዘርቶ ይቅማል፤ ዘሩ ይባረካል፤ ለአገር ለወገን የሚጠቅም፣ ለአባት ለእናቱ የሚታዘዝ፣ እግዚአብሔርን የሚያገለግል ይሆናል፡፡ ዘር የሚገኘው እግዚአብሔርን ከሚፈራና ትእዛዙን ከሚጠብቅ ሰው ነው፡፡ የጻድቃን ልጆች ሃይማኖት አላቸው፤ የጻድቃን ልጆች መልካም ሥነ ምግባር አላቸው፤ የጻድቃን ልጆች ክብር አላቸው፤ የጻድቃን ልጆች ሀብተ ሥጋ ሀብተ ነፍስ፣ በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስ አላቸው፡፡

ልጆቹ እንዲባረኩ እግዚአብሔር ለአብርሃም ቃል ኪዳን ሲሰጠው "በእውነት መባረክን እባርክሃለሁ፤ ማብዛትንም አበዛሃለሁ፤" ብሎ ከእርሱ በሚበልጥ በማንም ሊምል ስላልቻለ በራሱ ማለ ብሎ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ጠቅሶታል (ዕብ. 6÷13-14)፡፡ በኦሪት ዘፍጥረት የእግዚአብሔር መልአክ አብርሃምን ከሰማይ ሁለተኛ ጊዜ ጠራው፤ እንዲህም አለው፡- "እግዚአብሔር በራሴ ማልሁ ይላል፤ ይህን ነገር አድርገሃልና፣ አንድ ልጅህንም አልከለከልህምና በእውነት በረከትን እባርክሃለሁ፤ ዘርህንም እንደሰማይ ከዋክብትና እንደባሕር አሸዋ አበዛዋለሁ፤ ዘርህም የጠላቶችን ደጅ ይወርሳል፤ የምድር አሕዛብ ሁሉ በዘርህ ይባረካሉ፤ ቃሌንም ሰምተሃልና፤" ይላል (ዘፍ. 22÷15-18)፡፡

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም "እናንተ የነቢያት ልጆችና እግዚአብሔር ለአብርሃም በዘርህ የምድር ወገኖች ሁሉ ይባረካሉ ብሎ ከአባቶቻችን ጋር ያደረገው የኪዳን ልጆች ናችሁ" ብሏል፡፡ (የሐዋ. 3÷25)፡፡

አብርሃም ጻድቅ ስለነበር የተባረከ ልጅ ይስሐቅን አገኘ፤ ይስሐቅ ደግ ሰው ስለነበር የተባረከ ልጅ ያዕቆብን አገኘ፤ ያዕቆብ ደግ ሰው ስለነበር ክርስቶስ ከእርሱ ዘር ተወለደ፡፡ በአጠቃላይ ከአብርሃም፥ ከይስሐቅና ከያዕቆብ ዘር እመቤታችን ተገኘች፤ ከእመቤታችንም ክርስቶስ ተወለደ፡፡ አብርሃም፥ ይስሐቅና ያዕቆብ የተባረከ ዘርና ጻድቃን በመሆናቸው በቤተ ክርስቲያናችን ይከበራሉ፡፡

## ሃይማኖታዊ ምግባር

"ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደሆነ ሁሉ እንዲሁ ደግሞ ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው፡፡ (ያዕ. 2÷14-26)

እምነት ያለ ሥራ የክርስትና ሕይወትን የተሟላ ሊያደርግ እንደማይችልና ከእግዚአብሔር ዘንድ ጽድቅን ለማግኘት በጎ ምግባር አስፈላጊ መሆኑን በስፋት የሚያስተምር ነው፡፡ ለዚህም አብርሃምና ራኬብ እንደ መልካም ምሳሌ ሆነው ተጠቅሰዋል፡፡ እግዚአብሔር አብርሃምን ብዙ ጊዜ ስለ አነጋገረውና ማድረግ ያለበትንም ሁሉ በግልጽ ይነግረው ስለነበር፣ አብርሃም ስለ እግዚአብሔር ያለው እምነት የጠበቀ ነበር፡፡ እምነቱ ለእግዚአብሔር እንዲታዘዝ ስለአደረገውም የእምነት ብቻ ሳይሆን የምግባር ሰውም ነበር፡፡ የእግዚአብሔር ሰው የተባለበትና ለዚህ ዓለም አማንያንም መልካም ምሳሌ ለመሆን የበቃበት ዋና ምግባርም እግዚአብሔር አንድ ልጁን ይስሐቅን እንዲሠዋለት በጠየቀው ጊዜ ሳያመነታ የታዘዘውን ለማድረግ በማዘጋጀቱ ነበር፡፡

ሐዋርያው ያዕቆብ "አባታችን አብርሃም ልጁን ይስሐቅን በመሠዊያው በአቀረበ ጊዜ በሥራ የጸደቀ አልነበረምን? እምነት ከሥራ ጋር አብሮ ያደርግ እንደነበረ፣ በሥራም እምነት እንደተፈጸመ ትመለከታለህን? መጽሐፍም አብርሃም እግዚአብሔርን አመነ፤ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት፤ ያለው ተፈጸመ፤ የእግዚአብሔር ወዳጅም ተባለ፤" ሲል የተናገረውም ስለዚህ ነበር፡፡ አብርሃም እንዲህ አለ የእምነትና የምግባር ሰው ስለነበር በክርስቶስ የሚያምኑ የዓለም ወገኖች ሁሉ

በእምነት የአብርሃም ልጆች፣ የተስፋውም ወራሾች ተብለው ይጠራሉ (ገላ. 3÷7-10)።

በቅዱስ መጽሐፍ አብርሃምን የሚያመለክት ሌላም ታላቅ ቃል አለ፤ ይኸውም "በዘርህ የምድር አሕዛብ ሁሉ ይባረካሉ፤" የሚለው ቃል ነው (ዘፍ. 22÷18)። ይህም ቃል በክርስቶስ ተፈጽሟል። ክርስቶስ የተወለደው ከአብርሃም ዘር ነው። ዓለም በረከተ ሥጋንና በረከተ ነፍስን ያገኘውም በክርስቶስ ነው። ስለሆነም በክርስቶስ ያመኑ ሁሉ በእምነት የአብርሃም ልጆች ይባላሉ (ገላ. 3÷6-14)። ስለሆነም የክርስትና እምነት በዚህ ዓለም ኑሮ አብርሃምን መሆንን ይጠይቃል፤ ይኸውም ጽድቅን በእምነትና ምግባር ለማግኘት መብቃት ማለት ነው። በዕለቱ ምንባብ ረዓብም ለመልካም ሥነ ምግባር በምሳሌነት ተጠቅሳለች፤ ረዓብ ወይም ራኬብ በመልካም ምሳሌነት ለመጠቀስ የበቃችውም እስራኤል ከግብጽ ወደ ከነዓን በሚጓዙበት ጊዜ ኢያሱ የኢያሪኮን ምድር ለመሰለል የላካቸውን መልእክተኞች ከሚያሳድዷቸው የሀገሪቱ ሰዎች በቤቷ ደብቃ ከሞት ስለ አዳነቻቸው ነው (ኢያ. 2÷1-24)።

ከዚህ በላይ እንደተጠቀሰው አብርሃም በምሳሌነት የተገለጠው እምነትን ከምግባር ጋር አጣምሮ የያዘ የእግዚአብሔር ሰው በመሆኑ ሲሆን፣ ረዓብ ወይም ራኬብ ደግሞ የአብርሃም ዓይነት እምነት ሳይኖራት የሰውን ነፍስ ለማዳን በሠራችው በጎ ምግባር ነው። "ከእምነት የተለየ ምግባር የሞተ ነው" ከሚለው ቃል ሚዛናት የሚቻለውም የምግባርን ደግነት ነው፤ ምግባር የአብርሃም ዓይነት እምነት የሌላትን ሴት እንደ አብርሃም በመልካም ምሳሌነት ለመጥቀስ ያበቃ ከሆነ ድርጊቱ ሰው በሰውነቱ ብቻ ለሰው በጎ ማድረግ እንዲችል ሆኖ የተፈጠረ መሆኑን የሚያመለክት ነው። በተጨማሪም የረዓብ በጎ ሥራ የሴቶችን ርኅራኄ ከፍተኛነት የሚያመለክት ነው።

እመቤታችን የአምላክ እናት ለመሆን መመረጥዋን ከማወቋ በፊትም በሆን ኑሮዋ ለየትኛውም ዘመን ወጣቶች ደናግል መልካም አርአያነትና ምሳሌነት ያለው ነበር። ኅሊናዋ በዓለማዊ አሳብና ምኞት ያደፈ አልነበረም፡ ትሕትናና ርኅራኄ

ከንጽሕናና ቅድስና ጋር ተሟልቶ የተሰጣት ድንግል ናት፡፡ እግዚአብሔር እኔ ቅዱስ እንደሆንኩ፥ እናንተም ቅዱሳን ሁኑ ይላል (ዘሌ. 19÷2)፡፡ በዚህ አንጻር ሰዎች ከላይ እንደ እግዚአብሔር ከታች ደግሞ እንደ እመቤታችን ንጽሕናንና ቅድስናን ገንዘብ በማድረግ የወጣትነት ሕይወታቸውን ማምራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ እመቤታችን ከተለዩ የተለየች ስለሆነች ቅድስተ ቅዱሳን ተብላለች፡፡ እንደ እርስዋ ቅድስተ ቅዱሳን ለመሆን ባይቻልም፥ ቅድስት መሆን ይቻላል፡፡

## ሀ. ርኅራኄ

"የሚራሩ ብፁዓን ናቸው፤ እነርሱ ምሕረትን ያገኛሉና፡፡" (ማቴ. 5÷1-17) በቤተ ክርስቲያን ዘይቤ "አንቀጸ ብፁዓን" ይባላል፡፡ "የተራራ ላይ ስብከት" ብለው የሚጠሩትም አሉ፡፡ ሁለቱም ያስኬዳል፡፡ አንቀጸ ብፁዓን ተብሎ የሚጠራው በመንፈስ ነዳያን የሆኑ ብፁዓን ናቸው፤ ዛሬ የሚያዝኑ ብፁዓን ናቸው፤ የዋሃን ብፁዓን ናቸው፤ ስለ ጽድቅ የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው፤ የሚራሩ ብፁዓን ናቸው፤ ልባቸው ንጹሕ የሆነ ብፁዓን ናቸው፤ … ዕርቅን የሚያደርጉ ብፁዓን ናቸው፤ … ስለ ጽድቅ የሚሰደዱ ብፁዓን ናቸው… በማለት ምእመናን ከብፅዕና ደረጃ ለመድረስ የሚችሉት በምን ዓይነት በጎ ሥራ እንደሆነ በስፋት የሚናገር በመሆኑ ሲሆን "የተራራ ላይ ስብከት" የሚባለውም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን ትምህርት ለደቀ መዛሙርቱና ለሚከተለው ሕዝብ ያስተማረው በተራራ ላይ በመሆኑ ነው፡፡ ይህን ትምህርት ያስተማረባት ተራራም በአሁኑ ጊዜ "የብፁዓን ተራራ" ትባላለች በአሁኑ ጊዜ "ቅዱሳት መካናት" ተብለው ከሚጠሩት ቦታዎችም አንዷ ስለሆነች ወደ ኢየሩሳሌም በሚሄዱ ተሳላሚዎች ትጐበኛለች፡፡ ብፁዕ ማለት የተባረከ ማለት ነው፡፡

በዚህ ዘይቤ መሠረት የሚራሩ ብፁዓን ናቸው ማለት የተባረኩ ናቸው ማለት ይሆናል፤ በረከትም የሚገኘው ከእግዚአብሔር ነው፡፡ በዚህ መሠረት የሚራሩ ብፁዓን ናቸው ማለት በእግዚአብሔር የተባረኩ ናቸው ማለት ነው፡፡

"የሚራሩ ብፁዓን ናቸው" የሚለው ቃል ርኅራኄ የሰወን ልጅ "ብፁዕ፣ ብፅዕት" የሚያሰኝ ተግባር እንደሆነ በግልጽ ይታያል፡፡ ርኅራኄ፣ ምሕረት፣ ቸርነት፣ ለተጨነቀ ወይም ለተቸገረ ማዘንና ርዳታም ማድረግ ማለት ነው፡፡ እግዚአብሔር ርኅሩኅ ነው፡፡ ይህንም ነቢዩ ዳዊት "ሁልጊዜ አይቀሥፍም፤ ለዘለዓለም አይቈጣም፤ እንደ ኃጢኣታችን አላደረገብንም፥ እንደ በደላችንም አልከፈለንም፤ ሰማይ ከምድር ከፍ እንደሚል እንዲሁ እግዚአብሔር ምሕረቱን በሚፈሩት ላይ አጸና አባት ለልጆ እንደሚራራ እንዲሁ እግዚአብሔር ለሚፈሩት ይራራላቸዋል" ይላል (መዝ. 102÷9-14)፡፡ ለምሳሌ ነነዌ በነቢዩ በዮናስ ዘመን ኃጢአት የበዛባት ከተማ ነበረች፤ ኃጢአቷም እጅግ የበዛና የከፋ ስለነበር የእግዚአብሔር ቁጣ በነነዌ ላይ ነድዶ ነበር፡፡ ግን እግዚአብሔር ለፍጥረቱ ቸርና ርኅሩኅ ስለሆነ በሕዝቡ ላይ መቅሠፍትን ከማምጣቱ በፊት ሕዝቡ ከኃጢአቱ ተመልሶ ንስሓ ይገባ ዘንድ የሚያስጠነቅቅ ነቢይ ላከ፤ ለዚህ ተልእኮ የተመረጠው ነቢይ ዮናስ ነበር፡፡ ዮናስ ከከተማዋ እንደደረሰም እስከ ሦስት ቀን ድረስ ሕዝቡ ወደ እግዚአብሔር ተመልሶ ንስሓ ካልገባ የነነዌ ከተማ እንደምትጠፋ በማስጠንቀቅ ተናገረ፡፡ የነነዌ ሕዝብም የነቢዩ ዮናስን ቃል ሰምቶ ንስሓ ስለገባ እግዚአብሔር ለነነዌ ሕዝብ ምሕረት አደረገ፤ በዚህም ቸርነቱ እግዚአብሔር ለፍጥረቱ ያለወን ርኅራኄ ገለጠ (ዮና. 3÷1-10)፡፡

እግዚአብሔር ቸርና ርኅሩኅ አምላክ እንደሆነ አማኝያንም የእርሱን አርአያ በመከተል ቸርና ርኅሩኅ መሆን እንደአለባቸው በእምነታቸው ይገደዳሉ፤ ሐዋርያው ቅዱስ ጳወሎስ ለቈላስዩስ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን "እንግዲህ እግዚአብሔር እንደሚጣቸው ቅዱሳንና ወዳጆች ምሕረትንና ርኅራኄን፣ ቸርነትንና ትሕትናን፣ የወሀትንና ትዕግሥትን ልበሱት፤" (ቈላ. 3÷12) ሲል እንደተናገረው ለሰው ማዘንና መራራት ከሁሉም ሰው ይጠበቃል፡፡ በዚህ ዐይነት ርኅራኄ ብፁዓን ለመባል መብቃትም ታላቅ ጸጋ ነው፡፡ "የሚራሩ ብፁዓን ናቸው" የሚለው ቃል በጠቅላላ ለሁሉም ዘመን ትውልድ የተላለፈ ቃለ እግዚአብሔር ቢሆንም በተለይ ለአሁኑ ዘመን ትውልድ ታላቅ መልእክት አለው፡

ለሰው ልጅ ምድራዊወና ሰማያዊ ሕይወት መሠረቱ ፍቅር ነው፡፡ ፍቅር ከሌለ ሃይማኖትም የለም ማለት ነው፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስለ እምነት፣ ተስፋ፣ ፍቅር፣ አስፈላጊነት ከተናገረ በኋላ "ከእነዚህ የሚበልጠው ፍቅር ነው፤" ሲል የተናገረወም የፍቅር አለመኖር የእምነትን ጉድለት የሚያረጋግጥ መሆኑን ለመግለጽ ነው፡፡ ስለሆነም ፍቅር ከሌለ ሕይወት የለም፤ አይኖርም፤ ሕይወት ማለትም በመንፈሳዊወም ሆነ በሥጋዊው ዓለም ያለሥጋት፣ ያለፍርሀት፣ ያለጭንቀት በሰላምና በደስታ መኖር ማለት ነው፡፡

ፍቅር ካለ ደስታ አለ፤ ሰላም አለ፤ መግባባት፤ መተሳሰብ፤ መረዳዳት አለ፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው ፍቅር እንዲታገሱ ያደርጋል፤ ፍቅር ያስተዛዝናል፤ ፍቅር አያቀናናም፤ ፍቅር አያሳፍርም፤ ፍቅር ልበናን አያስታብይም፤ ለብቻዬ ተድላ ደስታ ላድርግ አያሰኝም፤ አንዱ በአንዱ ላይ እንዲቆጣ አያደርግም፤ አንዱ በሌላው ላይ ክፉ ነገርን እንዲያስብ አያደርግም፤ በበጐ ነገር እንጂ በክፉ ነገር ደስ አያሰኝም፤ በሁሉም ነገር ተስፋ እንዲኖር ያደርጋል፤ ፍቅር ያስከብራል እንጂ አያዋርድም (1ቆሮ. 13÷4-13)፤ ፍቅር ከአለ ይህን ዓይነት የሕይወት ኑሮ መኖር ከዐቅም በላይ አይሆንም፡፡ ፍቅር ማለት ይህ ማለት ከሆነ በአሁኑ ጊዜ ይህ ዓይነቱን ፍቅር መግለጽ የሚቻለው በምን ዓይነት መንገድ ነው?

ለዚህ ጥያቄ ትክክለኛወን መልስ ለማስጠት ከካህናት መጀመር ይቻላል፡፡ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአንድ ወቅት "ትወደኛለህን?" ሲል ለቅዱስ ጴጥሮስ ለአቀረበው ጥያቄና ቅዱስ ጴጥሮስም "እወድሃለሁ" ሲል ለሰጠው መልስ የተናገረው አጸፋ "ከወደድከኝ በጎቼን ጠብቅ" የሚል ነበር (ዮሐ. 21÷15-16)፡፡ ይህ ለሁሉም የቤተ ክርስቲያን መምህራን የተሰጠ መመሪያ ስለሆነ በአሁኑ ጊዜ ካህናት ምእመናንን ተግተወና ነቅተው በመጠበቅ ስለክርስቶስ ያላቸወን ፍቅር መግለጽ ይገባቸዋል፡፡

# ምዕራፍ ዐራት

## እምነትና ሥነ ምግባር

የሰው ልጅ "ይህ ይገባል፤ ይህ አይገባም፤" ይላል። ተገቢና ተገቢ ስላልሆነ የተከለከሉ ድርጊትን ይጠቅሳል። ተገቢና የማይገባ ብሎ በመናገሩም ራሱ የሰው ልጅ ከሥነ ምግባር ጋር የተሳሰረ መሆኑን ያመለክታል። እንደዚህ "ማድረግ ይገባል፤ እንደዚህ ማድረግ ፈጽሞ አይገባም" የሚሉት ቃላት ብዙ ጊዜ የምንሰማቸው እንደሆኑ ግልጥ ነው። የምንሰማቸውም መጽሐፍ ቅዱስን ከማንበብም ሆነ ከማንበብ፣ በእግዚአብሔር ከማያምነውም ሆነ ከማያምነውም ነው። ቤተሰባችንን ወይም የምንሠራበትን ቦታ ብንመለከት እነዚህ ዓረፍተ ነገሮች ምን ያህል የሕይወታችን ክፍል እንደሆኑ ለመረዳት አያቅትም። የማይገቡና የማይገቡ የሚባሉ ድርጊቶች ባይኖሩ ፍርድ ቤት፣ ዳኛና ምስክር፣ ዋስና ጠበቃ የሚባሉትም ባላስፈለጉ ነበር። እንግዲህ "የሚገቡና የማይገቡ" የምንላቸው ሁኔታዎች የሰው ልጅ ክፍል ስለሆኑ ሥነ ምግባር በሰዎች ላይ እንደተጣለ ጫና ተደርጎ እንዳይታይ ያስፈልጋል።

ሰውነቱ የሚሆንበትንና ክፋትን የሚሸነፍበትን መንገድ ማሳየት እንጂ በሰው ላይ ቀንበር መጫን አይደለም። ሥነ ምግባር የሚተምረው ሰው ከተሳሳተ ራስ ወዳድነት እንዲላቀቅ የሚጠራ መልእክት አለው። የሥነ ምግባር አስተምህሮ የሰውን ልጅ ተጨባጭ ሁኔታ በስፋት ስለሚዳስስ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የሰውን ልጅ ሁኔታ

ሳይደብቅና ሳያደበሰብስ በግልጥ የሚናገር የእግዚአብሔር ቃል "በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም፡ ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ" **1ቆሮ 6÷20** ነው።

## ሀ. እምነትና ሥነ ምግባር ያላቸው ዝምድና

እምነት ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው ተስፋ ስለ ምናደርገው ነገር የሚያረጋግጥ፣ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው ዕብ. **11÷1**

በጥንት ዘመን የነበሩ ሕዝቦች ለሥነ ምግባር ቦታ ቢኖራቸውም ከእምነት ጋር የተያያዘ አልነበረም። መጽሐፍ ቅዱስ ግን ሥነ ምግባርን ከእምነት ጋር ያጣምራል።

እምነት ማለት ከመልካም ሥነ ምግባር ሕግ ወደ ወጣው ሰው መልካም ዜና ይዞ ለመጣው እግዚአብሔር ከሰው በኩል የሚሰጠው ምላሽ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ጊዜ ይህን የእግዚአብሔርንና የሰውን መተሳሰር ኪዳን በሚለው ቃል ይገልጠዋል። ኪዳን ደግሞ የሰውን ተገቢ ምላሽና ተግባር ያካትታል። እምነት የእግዚአብሔር ስጦታ ነው። እምነት በሰው አካሄድና አኗኗር ላይ ተጽዕኖ አለው፤ የእግዚአብሔር ሕዝብም እንዴት መኖር እንዳለበት የኦሪት መጻሕፍት በስፋት ያስተምራሉ። እግዚአብሔር አንድ አምላክ እንጂ ብዙ አምላክ እንዳይደለ፣ ከፍጥረት ሁሉ በላይ የሆነ ፈጣሪ እንደሆነ፥ ለሰው ልጅም ክብርንና ነጻነትን የሰጠ አምላክ እንደሆነ ያስረዳሉ።

መጽሐፍ ቅዱስ የሚጠይቀው ሥነ ምግባር ከማዳን ታሪክ ጋር የተያያዘ ነው። እንግዲህ እምነት ከሁሉ አስቀድሞ ይህን የእግዚአብሔርን የማዳን ጥሪ መቀበል ነው። እምነት በሥራ መገለጥ እንዳለበት ያለ ሥራ ብቻውን እንደማይጠቅም ተገልጧል ያዕ. **1÷26**

ከዚያም እግዚአብሔር ፈጣሪና አዳኝ ስለሆነ የሰው ልጅ የሚሰጠው መልስ ሥነ ምግባርን ያካትታል። እግዚአብሔር በሲና ተራራ ላቆመው ኪዳን የእግዚአብሔር ሕዝብ አዎንታዊ መልስ ሰጥተዋል። ዘጸ. **19÷7-18** ዐሥርቱ ትእዛዛትም የዚህ ኪዳን ክፍል ናቸው።

"አትግደል" የሚለው እግዚአብሔር አምላክ ነው ከግብፅ ባርነት ሕዝቡን ነጻ ያወጣ አምላክ ነው። "አትስረቅ" የሚለውም ለሰው ልጅ በሙሉ ምድርን አስተዳድሯት ያለው አምላክ ነው። "አታመንዝር" የሚለውም የዮታን ሜልካምነትና የታማኝ ፍቅርን ታላቅነት ያወጀ አምላክ ነው። "ባልንጀራህን እንደ ራስህ ወደድ" የሚለውም ቃል "እኔ ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ" ከሚለው ቃል ማለየት የሌለበት መሆኑ ሚሳት የለበትም። ዘሌ. **19÷19**

የእግዚአብሔር ቃል ሥነ ምግባርን ከፍቅር ጋር ያዛምደዋል፡፡ ከሥነ ምግባር ትእዛዛት አንዱና ዋናው ፍቅረ እግዚአብሔር ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ፍቅረ ቢጽ ነው። ፍቅር የሕግ ሁሉ ፍጻሜ ነው ሮሜ **13÷8-10** "በመጀመሪያ ፍቅር ይኑርህ፤ ከዚህ በኋላም ሁሉን አድርግ።" ፍቅር ክፉ አያሠራም ለማለት ነው። የሥነ ምግባር ሕጎች ሁሉ በፍቅረ እግዚአብሔር እና በፍቅረ ቢጽ ማጠቃለላቸውን ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተናግሮአል። ማቴ. **22÷34-40**

መጽሐፍ ቅዱስ እንደዚሁ ተስፋን ከሥነ ምግባር ጋር ያጣምራል። ሰው ተስፋ በቆረጠ ጊዜ የሥነ ምግባር ጉድለት ይታይበታል። ራሱንና ባልንጀራውን በተመለከተ ሊያደርገው የሚገባውን ሁሉ ከማድረግ ቸል ይላል። የእግዚአብሔርንም ቸርነት ለማጠበበቅ አይታገሥም። መጽሐፍ ቅዱስ ግን ሦስቱ፦ እምነት፣ ተስፋና ፍቅር ጸንተው እንደሚኖሩና ከሁሉም ደግሞ ፍቅር እንደሚበልጥ፣ የሕጉም ሁሉ ማሰሪያ መሆኑን በአንጽንዖት ይናገራል። **1ኛ** ቆሮ **.13÷1-13** ማቴ **.22÷37-38**

## ለ. የሥነ ምግባር መርሖዎች

መጽሐፍ ቅዱስ ወስብስብ የሆነውን የሰውን ልጅ ሁኔታ በብዙ የሥነ ጽሑፍ ዐይነት ሥዕላዊ አድርጎ የሚያቀርብ በሥሪ ጽሑፈት ዐይነት እጅግ የበለጸገ መጽሐፍ ነው። ይህን አድርግ ይህን አታድርግ የሚል አንቀጽ ማውጫ መጽሐፍ አይደለም። ለምሳሌ ዐምስቱ ብሔረ ኦሪት ሕግጋትን ከታሪክ ጋር አጣምረው ያቀርቡልናል። የጥበብ መጻሕፍትም ከሰው ልጅ ረኽም ገጠመኝና ልምድ ጋር በማቅረብ በሐላፊነት እንድናስብ ይጋብዙናል። ጥሩ ምግብ እንዴት መሥራት እንደምንችል እያስተማረ ራሳችንን ወደ መቻል ያሳድገናል እንጂ ምግቡን አቅርቦ ከጥገኝነት ሳንወጣ

እንድንቀር አይተወንም። "ሥጋችሁ የክርስቶስ ብልቶች እንደሆኑ አታውቁምን? እንግዲህ የክርስቶስን ብልቶች ወስጄ የጋለሞታ ብልቶች ለአደርጋቸው አይገባም"፡፡ **1ቆሮ 6÷15**

## ሐ. ኅሊናዊ ሥነ ምግባር (ሕገ ልቡና)

ኅሊናዊ ሥነ ምግባር ወይም ሕገ ልቡና ከመጽሐፍ ቅዱሳዊው የሥነ ምግባር ሕግ በፊት የነበረ ነው። ስለሆነም "ሕግ ጠባይዓዊ፣ ሕገ ልቡና" እየተባለ ይጠራል። መጽሐፋዊ ሕግ የሰው ልጅ በኀጢአት ከወደቀ በኋላ የተሰጠ ሲሆን ሕገ ልቡና ከወደቀት በፊት የተሰጠ፣ በልብ የተሣለ ወይም የተቀረፀ ነው። ይሁን እንጂ የመጽሐፉ የልቡናው፣ የልቡናውም የመጽሐፉ ነው። "ሕግ ጠባይዓዊ ተውህበ እምነበ እግዚአብሔር ልዑል ቀዲሙ ዘጽሕፈሰ ተውህበ እምድኅረ ተዓድዎተ ትእዛዝ።" በመሆኑም ሕገ ልቡና እየተባለ ይጠራ ነበር ከዚህም ሌላ ራሱ ሰው በአርአያ እግዚአብሔር በሚፈጠሩ ለራሱ ሕግ ነው በኋላ ግን የእለት ዕለት ኑሮ እና እንቅስቃሴ የሥራ ምግባር ሕግ በጽሐፍ ተገልጦአል። ዘጸ. **20÷1-17**

"ጠባይዓዊ ሕግ ወይም ሕገ ልቡና አስቀድሞ ከልዑል እግዚአብሔር ተሰጠ፤ የተጻፈው ሕግ ግን ከትእዛዝ መተላለፍ በኋላ ተሰጠ።" **(ሚ. ይስ. አን. 2 ምዕ. 1 ገጽ 28-29)** ቅዱስ ጳውሎስ በሰው ልብ ያለው ወይም የተጻፈው ሕግ እንዲፈጸም የሚያስገድደውን ኀይል "ኅሊና" በማለት ገልጦታል። ሌሎችም ቅዱሳን አበው እንደ እርሱ ኅሊና ይሉታል። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ "እግዚአብሔር ሰውን በፈጠረ ጊዜ በውስጡ ሚዛናዊና ክፉን የሚፈርድ ኅሊናን ሰጠው" ይላል። በመቀጠልም "ሥነ ምግባራዊ ኅሊናን በሰው ልቡና ውስጥ ሁልጊዜ የሚሰማ የእግዚአብሔር ድምፅ ነው" ብሎታል።" ዮሐንስ አፈወርቅ በማዝ. **147** ትርጓሜ

ቅዱስ አውግስጢኖስ በመዝሙር **58÷1** ትርጓሜያቸው ላይ የሚከተለውን ብለዋል። "ሰዎች በልባቸው ውስጥ ተቀርፆ እያለ ማንበብ የተሳናቸውን ሕግ ጠባይዓዊ እግዚአብሔር በጽላት ጽፎ ሰጣቸው።"

መጽሐፍ ቅዱስ ኅሊናን በተመለከተ ትልቅ ትምህርትን ይሰጠናል። ኅሊና በሰው ሕይወት ወስጥ ትልቅ ቦታ እንዳለውያስተምሯናል። የሐዋ. **23÷1፣ 24÷16፣** ሮሜ **2÷15፣ 9÷1፣ 13÷5፣ 1**ጢሞ. **1÷5፣ 19** እና **2**ጢሞ. **1÷3** ።

ሆኖም ኅሊና ሲባል ሕግን ስንጥስ የሚወቅሰን ዳኛ ነው ማለት ብቻ አይ ደለም። ኅሊና በፊት የሠራናቸውን ድርጊቶች የምንገመግምበት ኃይል ብቻም አይደለም። ኅሊና ወደፊት ልንሠራቸው ያቀድናቸውንም ይመለከታል። ኅሊና የወደፊት ሁኔታዎችን፣ ወሳኔዎችንና ድርጊቶችን እንድንመዝን ያደርገናል። አግባብ ያላቸውን ቁም ነገሮችንና መርሖዎችን እንድንለይ፣ በነጻ ፈቃድም መርጠን በሕይወታችን እንድንተረጉም ያስችለናል።

አንዳንድ ጊዜ ሰው ስሕተት እየፈጸመ ኅሊናው ላይወቅሰው ይችላል፤ ይህም ሊሆን የሚችለው ኅሊናው በተገቢ ሁኔታ ሳይታነጽ ሲቀር፣ ወይም እንደ በድን የሚሰማው ሰው ሲሆን ነው፡፡ ስለዚህ ኅሊናው እንዲታነጽ ትምህርት አስፈላጊ ነው፡፡ **1**ጢሞ. **4÷2** ኅሊና ሰው ብቻውን ከአምላኩ ጋር የሚወያይበት መድረክ ነው፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ኅሊናን በማነጻትና ወደ ፍጹምነት ለማድረስ ሞተ፡፡ ዕብ. **9÷14፣ 1**ጴጥ. **3÷21** መጽሐፍ ቅዱስ አምልኮ ከሥነ ምግባር ጋር ተያይዞ እንደሚሄድ ይገልጻል፡፡ ነቢያትን ብንመለከት ንጹሕ የአምልኮ ሥርዐት፡-

- ከትክክለኛ ፍትሕና ጽድቅ፣
- ከፍቅርና እውነት፣ ድሃን ካለማስጨነቅ
- ጉቦ ከመቀበል (ከመስና)፣
- ደምን ከማፍሰስ፣
- በሐሰት ከመማል፣
- ከስርቆትና ከግድያ፣ ከዝሙት ንጹሕ ከመሆን፣
- ከፉውን ነገር ከማስወገድ፣
- መልካምን ከማድረግ ጋር መጣጣር አለበት ይላል፡፡ አሞጽ **5**፣ ኢሳ. **1÷11**፣ ኤር. **7**፣ መዝ. **14(15)**

ከዚህም ጋር ነቢያት ግፍ ለሚፈጸምበት ደምጽ አልባ ለሆነው ሕዝብ ቀዋሚያን ከመሆናቸው ጋር እግዚአብሔር አያየንም፣ አይመለከተንም፣ አይጐዳንም፣ ጌታችን ማን ነው የሚሉትንም ሕዝብ ይገሥጹ ነበር፡፡ **2ኛ.** ሳሙ. **12÷1-15**፣ **1ኛ** ነገ. **20÷17**

## መ. የሥነ ምግባር ማለኪያዎች

ማደግ፣ መቀየር ወይም ማለወጥ የሕይወት ክፍል ነው፡፡ በመንፈሳዊ ሕይወት የሥነ ምግባርም አመለካከታችን እንዲቀየር ወይም እንዲለወጥና ወደ ተሻለ ደረጃ እንዲደርስ ይጋብዘናል፡፡ ነገር ግን የሰው ልጅ በአንጻሩ በገዛ ራሱ ዓለምን እየበከላት መሆኑ ለሁሉም ግልጽ ነው፡፡ በዚህም አካሄድ የሰው ልጅ አግባብ ባልሆነ ኃላፊነት የጐደለው ሥነ ምግባር የሚኖርበትን ዓለም እያበላሸ ይገኛል፡፡ ለተተኪ ትውልድም የማትመች መተማመን የሌለባት ዓለም እያደረጋት ነው፡፡ ሥነ ምግባር ግን ተፈጥሮን እንድናከብር ይጋብዘናል፡፡ ለሰው ልጅ ጥቅምን የሚሰጡ ሕይወት ያላቸውና የሌላቸው ፍጥረታት ሁሉ ለዛሬ ሰዎች ጥቅም እንደሆኑ ለመጪውም ትውልድ ጠቃሚነታቸው እንዲቀጥል በጥንቃቄ መያዝና መንከባከብ የሥነ ምግባር ግዴታ ነው፡፡ ዘፍ. **1÷28-31**፣ ሆኖም ለሰው ሊደረግ የሚገባውን ፍቅርና እንክብካቤ ለሰው ጥቅም ይሆኑ ዘንድ ለተፈጠሩት ቁስና እንስሳት ማድረግ ተገቢ አይሆንም፡፡ ምክንያቱም ሰው ከፍጥረት በላይ ልቆ የተፈጠረ ነውና ነው፡፡

በዓለማችን የብዙ ደም መፍሰስ ምክንያት እየሆኑ ያሉት ትዕቢት፣ ቅንአትና ቁጣ፣ ቂምና በቀል፣ ሰሰኝነት፣ ራስ ወዳድነት፣ ዘረኝነት፣ ጉቦኝነት፣ እግዚአብሔር ያየኛል፣ ይመለከተኛልም አለማለት፣ ወዘተ..... ናቸው፡፡

ሥነ ምግባር ግን ትሕትናን፣ በሌሎች ዕድገት ደስ ማሰኘትን፣ ይቅርታን፣ የዕርቅ መንፈስን፣ ከፉን በከፉ ዐመጽን በዐመጽ አለመቃወምን፣ ቂምን መተውን፣ ለሰው ልጅ አለማበቀልን ያስተምረናል፡፡ የዚህም ዋናው አስተማሪ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ማቴ. **5÷38-48**

እንደዚሁም የተጠየቂነት መንፈስ መኖር ተገቢ መሆኑን፣ ታማኝነትን እግዚአብሔር ያየኛል ማለትን ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር ይፈርዳል ማለትንና እግዚአብሔር ከሁሉ በላይ መሆኑን ያስተምረናል፡፡

ስለዚህም ሰው በአርአያ ሥላሴ የተፈጠረ ስለሆነ የሥላሴን አርአያነቱን ጠብቆ መኖር ያለበት፣ ሰው ከሌላው ፍጥረት ሁሉ የከበረና የተወደደ በመሆኑ ክብሩንና ተወዳጅነቱን፣ ታማኝነቱንና ሥነ ምግባራዊ ሕይወቱን ጠብቆ መኖር አለበት፡፡

ሐሰት ተገቢ እንዳልሆነ የሚገልጡ ትምህርቶች ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ ቢገኙም ከእምነት ጋር የተጣመሩ ሆነው አይታዩም፡፡ ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስን ስንመለከት ሕይወት ያለው፣ ከእምነት ጋር የተያይዘ ነጥብን እናገኛለን፡፡ ኤፌ. **4÷25** ምክንያቱም ሕግ ፊደል ብቻ ሳይሆን ሕይወት የሚሰጥ መንፈስ መሆኑን ከመጽሐፍ ቅዱሳዊው ሥነ ምግባር ማግኘት እንችላለን፤ **2ቆሮ. 3÷6** በደስታ ለእውነት መቆምም ከዚህ ይመነጫል፤ ጽድቅን እንደ እህል መራብ፣ ፍትሕን እንደ ውኃ መጠማት ከዚህ ይመጣል፡፡ አዲሱ የክርስቶስ ሕግ በውጫዊ ነገር አይለካም፤ ወደ ወስጥ ዘልቆ የሚገባ ነው፡፡ ለፍቅር፣ ለሰው ልጅ እውነተኛ ደስታና ጥቅም ሲባል ሕይወትን እንኳ መሥዋዕት ማድረግ ተገቢ መሆኑን ያስተምራል፡፡ ዮሐ. **15÷12-13** የፍጹም ደስታና ሰላም ምንጩ ይህ ነውና፡፡

## ሠ. የሥነ ምግባር ግንባታ

መጽሐፍ ቅዱስ "በሐሰት አትመስክር" ይላል፡፡ ይህ ለፍትሕ ጽኑዕ መሠረት የሚሆን ትምህርት (ሥነ ምግባራዊ ሕግ) ነው፡፡ እንዲሁም "የሌላውን ገንዘብ አትመኝ" ይላል፡፡ ከዚህ የበለጠ የፀረ ሙስና መድኃኒት (ፀረ ሙስና) ያለ አይመስልም፡፡ ሁሉም ሰው ፍቅርና ደስታን ትክክለኛ ፍትህንም ይፈልጋል፡፡ ክብሩን ነፃነቱንና መብቱን ሁሉ ሊያጣ አይፈልግም፤ ሌላው ደግሞ ይህን ለማሳጣት የሚያደርገው ተጽዕኖ መከልከል ግዴታው ነው፡፡ ባልጀራህ በነፃ ሊያገኘው የሚገባውን መብት በገንዘብ (በጉቦ) እንዲገዛው ማድረግ የለበትም፡፡ ጉቦ ራስን የሚያዋርድ ግለሰቡንና ማኅበረሰብን የሚጎዳ ነው፡፡ ዘጸ. **23÷8-9**፣ ምሳ. **28÷25** "እርስ በርሳችሁ ይቅር ተባባሉ" ይላል፡፡ ከዚህ የበለጠ የበቀል

መድኃኒት የት ይገኛል? ይቅርታ፣ መቻቻል ከሌለ ደም ደምን እየጠራ፣ ዐመፅ ዐመፅን እየወለደ ማነለቅት ወደ ሌለው ጥፋት መዳዝ ይሆናል፡፡ "በአንተ ላይ እንዲደረግ የማትፈልገውን በሌላው ላይ አታድርግ" ይላል፡፡ ከዚህ የተሻለ የቢሮክራሲ መድኃኒት የት ይገኛል፡፡ የእግዚአብሔር ቃል ስለ ጾታ ሚልካምነት፣ ስለ ሰው አካል ክቡርነት፣ ስለ ሰው ሥነ ምግባራዊነትና ኃላፊነትን ስለ ተላበሰ ፆታዊ ጥምረት "አታመንዝር" ይላል፡፡ በዝሙት ምክንያት ለሚከሰተው በሽታ ሁሉ ከዚህ የበለጠ መድኃኒት ምን አለ?

ሰው የእግዚአብሔር አርአያና ምሳሌ መሆኑን ያስተምራል ዘፍ. **1÷26-27** ከዚህ ሌላ ለሰው ምን ክብር አለው፡፡ በአንጻሩም ሰው በሥነ ምግባሩ ሕፀፅ ምክንያት እንደ እንስሳ መሆኑን ይናገራል፡፡ እንዲያው በዘመናችን ከእንስሳም በታች ሆኗል፡፡ ከዚህም የከፋ የሰው ወርደት የለም፡፡ መዝ. **48÷12**፡፡

"ልጆች ወላጆቻችሁን አክብሩ፣ ወላጆችም ልጆቻችሁን አታስቈጡ፤ ሠራተኞች በአሠሪዎቻችሁ ታዘዙ፣ አሠሪዎችም ሠራተኞችን አትበድሉ፣ ዜጎች አግባብ ያላቸውን ሃይማኖትን፣ ባህልን፣ የሰው ክብርን ለሚጠብቁ ባለ ሥልጣናት አክብሩ" ይላል፡፡ ኤፌ. **6÷1-9**፣ ሮሜ **13÷7** ዛሬ ዓለም እያጣው ያለው የቤተሰብ ሥነ ምግባራዊ አመራር፣ የማኅበረ ሰብእ ሰላማዊ ሕይወት ትምህርት ይህ አይደለምን? የዘመኑን ትወልድ አደጋ ላይ ጥሎታል፡፡ ወቅቱ አሁን ነው በእነዚህ ላይ ቤተክርስቲያን እንደብሉይ ኪዳን ነቢያትና እንደ ሐዲስ ኪዳን ሐዋርያት በኃይል ድምጽዋን ማሰማት ይኖርባታል፡፡ ኅብረተሰቡ ሚዛን ከተለቀቀ የቤተሰብ አቅዋም ይናጋል፣ የጸና ጋብቻ ቀርቶ የመጣከር ጋብቻ ፈጣን የሆነ መፋታት፣ ልጆች እንዲበተኑ ምክንያት መሆን፣ ራስን መግደልና ሌሎችን ይዞ መጥፋት ሊከሰት ይችላል፤ እየተከሰተም ነው፡፡

ሥነ ምግባር ዐሠርቱ ትእዛዛት በሚጠቃለሉባቸው "አምላክህ እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ፣ በፍጹም ኃይልህ ወደደው፡፡ ባልንጀራህንም እንደ ራስህ ወደደው፡፡"

በተባሉት ፍቅረ እግዚአብሔርና ፍቅረ ቢጽ ይጠቃለላል፡፡ እንደ ጌታችን መድኃኒታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርት በእነዚህ በሁለቱ ዐበይት የሥነ ምግባር ሕግጋት ተጠቃልለዋል፡፡ ከዚህም ጋር ጌታችን በአንቀጸ ብፁዓን የተናገራቸው ስድስት ሕግጋተ ወንጌል ለመጽሐፍ ቅዱሳዊው ሥነ ምግባር ፍጹም ናቸው፡፡ ማቴ. **22÷35-38**፡፡

"ፍቅራችሁ ያለ ግብዝነት ይሁን፡፡ ከክፉ ራቁ፣ በጐውንም ያዙ፣ ለጽድቅ አድሉ፣ እርስ በእርሳችሁ በወንድማማችነት መዋደድ ተዋደዱ፣ የምትራሩም ሁኑ፡፡ እርስ በእርሳችሁ ተከባበሩ፡፡ ወላጆቻችሁን አክብሩ፣ ለሥራ ከመትጋት አትለግሙ በመንፈስ ሕያዋን ሁኑ፡፡ ለእግዚአብሔር ተገዙ፣ በተስፋ ደስ ይበላችሁ፣ በመከራ ታገሡ፣ ለጸሎት ትጉ፣ ችግረኞችን ለመርዳት ተባበሩ፣ እንግዳ መቀበልንም አዘውትሩ፡፡"

"የሚያሳድዷችሁን መርቁ፣ መርቁ እንጂ አትርገሙ ደስ ከሚለው ጋር ደስ ይበላችሁ፡ ከሚያዝነው ጋር እዘኑ፣ እርስ በእርሳችሁም በአንድ ሀሳብ ተስማሙ፡ የትዕቢትን ነገር አታስቡ፣ ራሱን ዝቅ የሚያደርገውን ሰው ምሰሉ፡፡ እኛ ዐዋቂዎች ነን አትበሉ፡፡ ክፉ ላደረገባችሁም ክፉ አትመልሱለት፡፡ በሰው ሁሉ ፊት በጐውን ተነጋገሩ ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ፡፡ ወንድሞቻችን፣ ራሳችሁ አትበቀሉ፣ ቁጣን አሳልፋአት፡፡ በቀል የእኔ ነው፣ ብድራትንም እከፍላለሁ ይላል እግዚአብሔር" ተብሎ ተጽፎአልና፡፡ ጠላትህ ቢራብ አብላው፣ ቢጠማም አጠጣው፡፡ ይህን ብታደርግ በራሱ ላይ የእሳት ፍም ትከምራለህ ክፉውን በሚልካም ሥራ ድል ንሣው እንጂ ክፉውን በክፉ ድል አትንሣው"፡፡ ሮሜ **12÷9-21**

# ምዕራፍ አምስት

## የካህናት ተልእኮ

"በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቋት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ፡፡" (የሐ. ሥራ 20÷28)

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም ባደረገው በሦስተኛ ጉዞው ሚሊጢን የሚባል ሀገር ቆይታ አድርጎ ነበር፡፡ በዚያ ሳለ የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን መሪዎችን አስጠርቶ የሚከተለውን ምክር ሰጥቷቸዋል፡፡

ራሱ ቅዱስ ጳውሎስ ከሄደ በኋላ ለመንጋው ማለት ለምእመናን የማይራሩ ጨካኞች ተኩላዎች መናፍቃን ከመካከላቸው ተነሥተው ለምእመናን ጠማማ ትምህርት እያስተማሩ እንደሚያሳስቱ አስቀድሞ በመንፈስ ቅዱስ ስለተረዳ የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለራሳቸውና ለምእመናን ሁሉ እንዲጠነቀቁ ተግተውም ራሳቸውንና ሌላውን እንዲጠብቁ በአጽንዖት መክሯቸዋል፡፡ ከዚህም ጋር ቅዱስ ጳውሎስ መሪዎቹ እግዚአብሔርን እንዳይክዱ ቃሉንም እንዳይለውጡ አደራ ብሏቸዋል፡፡ በተጨማሪም ቅዱስ ጳውሎስ ራሱ ተግባረ ዕድ እየሠራ ራሱንና ከእርሱ ጋር የነበሩትን ይረዳ ነበር እንጂ ከማንም ወርቅና ብር ልብስም ለመቀበል እንዳልፈለገ ሁሉ የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን መሪዎችም እየሠሩ ራሳቸውን ሊረዱ የሚገባቸውን መሆኑንና ሌሎችንም መርዳት እንዳለባቸው ምክር ሰጥቷቸዋል፡፡ ምክንያቱም ይላል ቅዱስ ጳውሎስ "በድካማችንና በሥራችን በሽተኞችን ልንረዳቸው ይገባናል" ጌታችን ኢየሱስ "ከመቀበል ይልቅ የሚሰጥ ብፁዕ ነው" ያለውንም ማስታወስ እንደሚገባቸው የሚጨርሻ ምክሩን በማለገስ በጸሎት ተሰናብቷቸዋል፡፡ ምንም እንኳ "ለሚያገለግል ምግቡ ይገባዋል" ቢባልም (ማቴ. 10÷10) አንድ የሃይማኖት መምህር ወይም ካህን በሃይማኖት ስም ለሌሎች ሸክም ሆኖ መኖር የለበትም፡፡ ስለዚህም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ

ለተሰሎንቄ ምእመናን ሲመክር ስለ ራሱና ስለ ወንጌል ትምህርት ጓደኞቹ የተናገረውን ቃል ማስተዋል ያስፈልጋል፡፡ "ወንድሞቼ ሆይ፣ ከእኛ እንደተቀበለው ሥርዓት ሳይሆን ያለ ሥርዓት ከሚሄድ ወንድም ሁሉ ትለዩ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናዝዛችኋለን፡፡ እኛን ልትመስሉ እንዴት እንደሚገባችሁ ራሳችሁ ታውቃላችሁና፡፡ በእናንተ ዘንድ ያለ ሥርዓት አልሄድንምና፡፡ ከእናንተ በአንዱ ስንኳ እንዳንከብድበት ሌሊትና ቀን በድካምና በጥረት እየሠራን እንኖር ነበር እንጂ ከማንም እንጀራን እንዲያው አልበላንም፡ ይህም እኛን ልትመስሉ ራሳችንን እንደ ምሳሌ እንሰጣችሁ ዘንድ ነበር እንጂ ባለ ሥልጣን ስለሆን አይደለም፤" (2ተሰ. 3÷6-9)፡፡

በትምህርተ ሐዋርያትም (በዲድስቅልያ) አንድ የሃይማኖት መምህር ሃይማኖትን በሚያስተምረው ሰው ቤት ብዙ ጊዜ ቢኖር ክርስቶስን የንግድ ዕቃ ያደርገዋል ተብሏል፡፡ (ዲዳሐ) በመሆኑም የወንጌል መምህራን ራሳቸውንም ሌሎችንም መሥራት የሚችሉትን ለመርዳት ሥራ መሥራት እንደሚያስፈልግ ሊገነዘቡ ይገባል፡፡ በዚህ የቅዱስ ወንጌል ምዕራፍ ጌታችን ራሱን በቸር ጠባቂ መስሎ ሲናገር ምእመናንን ደግሞ በበጎች መስሎ ተናግሯል፡፡ (ዮሐ. 10÷1-18)

በመልካም እረኛ የተመሰለው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምእመናን ድምፁን ለይተው እንዲያውቁትና እንዲሰሙት እንዲከተሉትም ያስተምረናል፡፡

የኢየሱስ ክርስቶስ ድምፅ በቅዱስ መጽሐፍ በተለይም በአራቱ ወንጌላውያን በሚገባ ተመዝግቦ የደረሰን ስለሆነ ድምፁን ለመስማት ችግር የለብንም፡

ይህ ድምፅ የእግዚአብሔር አብም ድምፅ ነው፤ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም ድምፅ ነው፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ወልድ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮርዳኖስ በተጠመቀ ጊዜ፣ በደብረ ታቦርም መለኮታዊ ክብሩን በገለጸ ጊዜ "የሚሏችሁን ስሙ" ብሎ ነግሮናልና፤ (ማቴ. 3÷16-17፣ 17÷5)፡፡ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም በራሱ ላይ በርግብ አምሳል ወርዶ ነገሩን አጽድቆልናል፡፡ ከዚህ በመነሣት ይህ ድምፅ መለኮታዊና ሰማያዊ ድምፅ ነው፤

ብለን ማምንና መቀበል ከእኛ ይጠበቃል (2ጴጥ. 1÷16-20)፡፡ በዚህ ምዕራፍ ምእመናን የጠበቂያቸው የኢየሱስ ክርስቶስ ድምፅ ካልሆነ በቀር የሌላውን ድምፅ እንዳይሰሙና እንዳይከተሉ ይልቁንም ከእርሱ እንዲሸሹ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷል፡፡ ምክንያቱም ከኢየሱስ ክርስቶስ ድምፅ የተለየ ሌላ ድምፅ ሊያሳስት፣ ሊያጠፋና ሊጎዳ ካልሆነ እነርሱን የሚጠቅም አይደለምና፡፡ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ድምፅ ግን የተትረፈረፈ ሕይወት ለምእመናን ሊያስገኝ የሚመጣ ድምፅ ነውና ጆሮአቸውን ከፍተው ሊያደምጡ ይገባል (ማቴ. 13÷9)፡፡

"እንደ በጎች ትቅበዘበዙ ነበር፤ አሁን ግን ወደ ነፍሳችሁ እረኛና ጠባቂ ተመለሱ፡፡"

ቃባ የያዘው በግ ከመንጋው ሰለይ ይቅበዘበዛል፤ ቃባ የያዘውን በግ ከመንጋው ለይተው በደረቅ ቦታ አስረው ደረቅ ሣርና ጥሩ ውኃ ይመግቡታል፤ ሲድን ታቅፈው ወስደው ከመንጋው ይቀላቅሉታል፤ ከመንጋው መለየቱ፣ አዳም ከማኅበረ መላእክት የመለየቱ፣ በደረቅ ሥፍራ አስረው ደረቅ ሣርና ጥሩ ውኃ መመገባቸው አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን በሲኦል በእደ እግዚአብሔር ተይዞ የመኖሩ፣ ሲድን ወስደው ከመንጋው መቀላቀላቸው፣ ባሕርዩን ባሕርይ አድርጎ፣ ጽንዐ ነፍስን ሰጥቶ አጽንቶ ወደ ገነት የመመለሱ ምሳሌ ነው፡፡ የጻድቃን ነፍሳት በሲዖል ሲኖሩ የሲዖል እሳት ወላፈን አላገኛቸውም "የጻድቃን ነፍሳቸው በእግዚአብሔር እጅ ወስጥ ናት፤ የሥቃይ ወላፈንም አልነካቸውም" ተብሏልና፡፡ (1ጴጥ. 2÷25 የአንድምታ ትርጓሜ)

ይህንንም በተመለከተ ነቢዩ ኢሳይያስ እንዲህ ይላል፡- "እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን፤ ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ፤ እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ"፤ (ኢሳ. 53÷6)፡፡ ሕዝቅኤልም "በጎቼ እረኛን በማጣት ተበተኑ፣ ለምድርም አራዊት ሁሉ መብል ሆኑ፤ ተበተኑም" ይላል (ሕዝ. 34÷5)፡፡

ቤተ ክርስቲያን ለበጎች (ምእመናን) ደኅንነት ሕይወቱን አሳልፎ የሰጠ ቸር እረኛ ኢየሱስ ክርስቶስ በበትረ መስቀሉ የጠበቃቸው ምእመናንን የሚያስተምሩባት አፀድ፣ የምእመናንን መንፈሳዊ ሕይወት በንስሐ መዛሪያ እየሚሙ ከኃጢአት ደዌ የሚፈወሱባት የጤና ማእከል፣ (ማር. 6÷12-13፣ ዮሐ. 3÷6) መዳንን ለሚሹ ሁሉ የሚበቃ ማጠለያና መመላለሻዎች ያሏት የፈውስ ቦታ ቤተ ሳይዳ ቤተ ክርስቲያን ናት (ዮሐ. 5÷2)፡፡

"በእናንተ ዘንድ ያለው የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፡፡"

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ይህን መመሪያ የሰጠው ለካህናት ነው፡፡ የእግዚአብሔር መንጋ የተባሉ የእግዚአብሔር ወገኖች፣ የክርስቶስ ተከታዮች የሆኑ ምእመናን ናቸው፡፡ (1ጴጥ. 5÷2-9)

ምእመናንን የመጠበቅ አደራ አስቀድሞ ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተቀበለ ራሱ ጴጥሮስ ነው (ዮሐ. 21÷15-17)፡፡ እሱ ደግሞ በበኩሉ የጥበቃውን ኃላፊነት በሥሩ ላሉት ቀሳውስት ያስተላልፋል፤ የጥበቃው ሥራ ከቄስ እስከ ፓትርያርክ እና ሊቃነ ጳጳሳት ያሉትን ካህናት ሁሉ የሚያጠቃልል ነውና፡፡

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ፡- "አሁን ራሳችሁን ጠብቁ፤ ምእመናንንም ጠብቁ፤ በደሙ የዋጃትን የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን (ምእመን) ትጠብቁ ዘንድ መንፈስ ቅዱስ (እግዚአብሔር) እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ሾሟችኋል፤" ብሏል (የሐዋ. ሥራ 20÷28)፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንደ ቅዱስ ጴጥሮስ በሥሩ ላሉት ጳጳሳት ይህንን ተመሳሳይ መመሪያ ሰጥቷል፡፡ ጌታ ለቅዱስ ጴጥሮስ፣ ቅዱስ ጴጥሮስና ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ በሥራቸው ላሉ ካህናት የሰጡት መመሪያ የምእመናንን የጥበቃ ሥራ የሚያጠናክር ነው፡፡

ካህናት እግዚአብሔር ራሱ የራሱን በጎች ይጠብቁለት ዘንድ የሚጠራቸውና የወደዳቸው አገልጋዮች ናቸው (ዮሐ. 15÷16)፤ እንዲሁም የተሰጣቸው ሹመት ዓለም ከሚሰጠው የተለየ ምድራዊና ሰማያዊ ጸጋ ነው (ማቴ. 16÷19፣ 18÷18)፡፡ በዚህ በተሰጣቸው ሹመት ደግሞ ሊያከናውኑት የሚገባ ተግባርና

ኃላፊነት አለ፤ ይህም የእግዚአብሔርን የመንግሥት ወንጌል ይሰብኩ ዘንድ ነው። የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዲሰብኩና ድውዮችን እንዲፈውሱ ላካቸው (ሉቃ. 9፥1-6)።

ምእመናንን የሚጠበቂያው መሣሪያም ወንጌል ነው፤ ወንጌል የተሚሂ በመናፍቃን አይሰረቅም፤ ወንጌል የተሚሂ ሕገ እግዚአብሔርን አይተላለፍም፤ አይሰርቅም፤ አይዋሽም አይቀማም።

"አቤቱ ፈጥነህ ስማኝ፣ ሰውነቴ አልቃለች፣
ፊትህን ከእኔ አትመልስ፣
ወደ ጉድጓድም (መቃብር) እንደሚወርዱ አልሁን፣
አንተን ታምኛለሁና፣
በማለዳ ምሕረትህን አሰማኝ።" (መዝ. 142፥7-8)

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለደቀ መዝሙሩ ለጢሞቴዎስ የመጀመሪያውን መልእክት ሲጽፍለት ስለ ኦሪትና ስለ ወንጌል፣ ስለ ሥጋዊና መንፈሳዊ ሕይወት ትምህርት የሆነውን ይህን መመሪያ ሰጥቶታል። (1ጢሞ. 4፥7)

ጢሞቴዎስ ማን ነው? ጢሞቴዎስ ሐዋርያው ጳውሎስ በልስጥራን ከተማ ያገኘው ወጣት ነው፤ አባቱ የግሪክ ሰው ሲሆን እናቱ አይሁዳዊት ነበረች (የሐዋ. 16፥1-3)። ሴት አያቱና እናቱ ክርስቲያኖች ነበሩ፤ ራሱ ወጣቱም ቅዱሳት መጻሕፍትን ተምሮ ነበር (2ጢሞ. 1፥5፣ 3፥14-15)። የጳውሎስ የመንፈስ ቅዱስ ልጅ ነበረ። ሐዋርያው በሄደበት ሁሉ አብሮ ይሄድ ነበር፤ በኋላም ወደ ቆሮንቶስና ወደ ተሰሎንቄ መልእክተኛ ሆነ፤ በኤፌሶንም ለሐዋርያው እንደራሴ ሆኖ ቆየ (1ቆሮ. 4፥17፣ 1ተሰ. 3፥1-8፣ 1ጢሞ. 1፥3)። በአንዳንድ የጳውሎስ መልእክቶች ላይ የጢሞቴዎስ ስም እንደ አባሪ ደራሲ ተጨምሮ ተጽፏል (2ቆሮ. 1፥1፣ ፊል. 1፥1፣ 1ተሰ. 1፥1፣ 2ተሰ. 1፥1)።

ሐዋርያው ጳውሎስ ሁለት መልእክቶችን ለጢሞቴዎስ ጽፎለታል። (1ኛ እና 2ኛ ጢሞ.) አንድ ጊዜ መታሰሩም ታውቋል (ዕብ. 13፥23) ጢሞቴዎስ

በኤፌሶን ሳለ ጳወሎስ የመጀመሪያውን መልእክት ጻፈለት፣ ዘመኑ 63 ዓ.ም. ገደማ ይሆናል፡፡ ሐዋርያው ወደ ኤፌሶን ሊመጣ ተስፋ አድርጎ ነበር፤ ግን ዘገየና ጢሞቴዎስን ሊያበረታ በአንዳንድም የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ጉዳይ ሊመክረው ጻፈለ (1ጢሞ. 1÷3-7፣ 3÷14-15፣ 14÷13)፡፡

በዚህ መሠረት ስለ ራሱ አኑዋኑዋር የተሰጠ ምክር ነው፡፡ "እግዚአብሔርን ለመምሰል ራስህን አስለምድ" ሲለው ምን ማለቱ ነው? ሐዋርያው በሌላ ቦታ "እኔ ክርስቶስን እንደ መስልሁት እናንተም እኔን ምሰሉ" ብሎ ለቆሮንቶስ ሰዎች እንደ አስተማረው (1ቆሮ. 11÷1፣ 4÷16) እግዚአብሔርን ለመምሰል ራስን ማለማመድ ማለት ለጽድቀ ወንጌል መገዛት ነው፤ ፈሪሀ እግዚአብሔርን ተግባራዊ ማድረግ ነው፡፡

ሰውነትን ለሥጋዊ ነገር ማስለመድ ለጥቂት ጊዜ ይጠቅማል ማለቱ የሥጋ ደስታ ለጊዜው የሚጠቅም ይመስላል ዘላቂነት ግን የለውም፤ በወንጌል የታዘዘውን የጽድቅ ሥራ መሥራት ግን በሥጋም በነፍስም ይጠቅማል፤ በሥጋም በነፍስም በሕይወት ለመኖር ያበቃል፡፡ ለትእዛዘ ወንጌል የማገዛ ሁሉ ኃጢአት አይሠራም፡

"በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ፤ እኔም አውቃቸዋለሁ፤ ይከተሉኝማል፤ እኔም የዘለዓለምን ሕይወት እሰጣቸዋለሁ፤ ለዘለዓለምም አይጠፉም፤ ከእጄም ማንም አይነጥቃቸውም፤" (ዮሐ. 10÷25)፡፡

ይህ ቃል የተነገረው ክርስቶስንና ምእመናንን ከእረኛና ከበግ መንጋ ጋር በማነጻጸር በጎች በእረኛ እንደሚጠበቁ ምእመናንም ክርስቶስን ያህል ቸር ጠባቂ ያላቸው መንጋዎች መሆናቸውን ለማመልከት ነው፡፡ ቅዱስ መጽሐፍ ራሱ ክርስቶስንም የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ ይለዋል (ዮሐ. 1÷29፣ ራዕ. 5÷6-12)፡፡ ሆኖም በዚህ ምንባብ በበጎች የተመሰሉት ምእመናን ናቸው፡፡ ሰው በብዙ ምክንያት በበግ ተመስሏል፡፡ ለዚህም ዋናው ምክንያት በግ ንጹሕና የማይጎዳ የዋህ እንስሳ በመሆኑ ነው፡፡ ጌታችን ኢየሱስ

ክርስቶስም በማቴዎስ ወንጌል "የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡባችሁ በውስጣቸው ግን ነጣቂዎች ከሆኑ ከሐሰተኞች ነቢያት ከመናፍቃን ተጠንቀቁ፤" (ማቴ. 7÷15)፤ ሲል ተናግሯል፡፡ የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡ ነጣቂ ተኩላዎች ተጠንቀቁ የሚለው ቃል የሚገልጸው ደግ መስለው በመቅረብ ምእመናንን የሚያሳስቱ ሐሰተኞች ነቢያት መኖራቸውን ነው፡፡ በመሆኑም ምእመናን እረኛ የሌላቸው በጎች ሆነው እንዲኖሩ የክርስቶስ ፈቃድ አይደለም፡፡ በዚህም ምክንያት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብዙ ሕዝብ ባየ ጊዜ እረኛ እንደሌላቸው በጎች ተጨንቀው፣ ተጥለውም ነበርና አዘነላቸው፤ በዚያ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን "መከሩስ ብዙ ነው፣ ሠራተኞቹ ግን ጥቂቶች ናቸው፡፡ እንግዲህ የመከሩን ጌታ ወደ መከሩ ሠራተኞችን እንዲልክ ለምኑት፤" (ማቴ. 9÷36) ሲል እንደተናገረ ቅዱስ መጽሐፍ ይገልጣል፡፡ "እረኛ የሌላቸው በጎች" የተባሉት እስራኤል ናቸው፤ በኋላም ሐዋርያትንና ሰብአ አርድእትን በማስነሣት የላካቸውን እስራኤልን እረኛ ያላቸው በጎች እንዲሆኑ አድርጎ ነበር፡፡ ሆኖም ሁሉም እስራኤል የክርስቶስ መንጋዎች ለመሆን ሳይበቁ ቀርተዋል፡፡ ላመኑት ግን የእግዚአብሔር ልጆች ለመሆን የሚያበቃ ሥልጣን ሰጥቷቸዋል (ዮሐ. 1÷12)፡፡ በኋላም በዕለተ ምጽአት በክርስቶስ ቀኝ የሚቆሙት ምእመናን በበጎች ይመሰላሉ (ማቴ. 25÷33)፡፡

ምእመናን በበጎች የተመሰሉት ከእስራኤል በጎች አንጻር ነው፡፡ የኢየሩሳሌም በጎች የእረኞቻቸውን ድምፅ ያውቃሉ፤ እረኛቸው የሚያሰማቸው ድምፅ ምን ማለት እንደሆነ ዘይቤውን ያውቃሉ፤ በመሆኑም እረኛው አንድ የሆነ ድምፅ ሲያሰማቸው ይሰበሰባሉ፡፡ ሌላ የሆነ ድምፅ ሲያሰማቸው ደግሞ ለግጦሽ ይበተናሉ፡፡ በሀገራችን በጎች ወደተፈለገው ቦታ የሚሄዱት በእረኛ እየተነዱ ነው፤ በኢየሩሳሌም ግን እረኛቸው ለበጎች የሆነ ድምፅ አሰምቶ ወደፊት ሲሄድ በጎቹ ይከተላሉ (ዮሐ. 10÷4)፡፡ በክርስትና ዘመን ከምእመናን የሚፈለገውም ይህ ዓይነት ዕውቀት ነው፤ የክርስቶስ መንጋዎች እንደመሆናቸው መጠን የእረኛቸው የክርስቶስን ድምፅ በመስማት እሱን መከተል ይጠበቅባቸዋል፡፡ "በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ፤ እኔም አውቃቸዋለሁ፤ ይከተሉኛማል፤ እኔም የዘለዓለም

ሕይወትን እሰጣቸዋለሁ፤ ለዘለዓለምም አይጠፉም፤" ሲል በተናገረው ቃል መሠረት የዘመኑ ምእመናንም የዘለዓለም ሕይወትን ለማታደል የሚበቁት የእረኛቸው የክርስቶስን ድምፅ ሰምተው እሱን መከተል ሲችሉ ነው፤ "መከተል" ማለትም ከክርስትና እምነትና ምግባር ከምግባረ ወንጌል በተለያዩ ወጥምብሮች ሳይናወጡ በሕግና በአምልኮት ጸንቶ መኖር ማለት ነው፡፡ "በሰማይ የሚጸድቅ በምድር ያስታውቃል፤" እንደሚባለው አንድ ሰው ለዘለዓለማዊ ሕይወት የታደመ ከሆነ ምልክቱ በዚህ ዓለም ሳለ መታየት ይኖርበታል፡፡ በዚህ ዓለም ሊኖረው የሚገባው ሥጋዊና መንፈሳዊ ሕይወት የተሟላ ካልሆነ የዘለዓለም ሕይወትን ተስፋ ማድረግ እንዴት ይችላል?

እንደ ማረጃም ከምንጠቀምባቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅሶች በዚህ አጋጣሚ ሁለቱን ብቻ ብናወሳ የምንነጋገርበትን ፍሬ ሀሳብ ግልጽ ያደርግልናል፡፡

1. በነቢየ እግዚአብሔር ኢሳይያስ (61÷1-2) "ልባቸው የተሰበረውን እንድፈውስ፣ የተጨነቁትን ነጻ እንዳወጣ ለታሰሩትም ነጻነትን እንዳበስር ልኮኛል፤" የሚለውን፣
2. በትንቢተ አሞጽ 3÷7 ላይ "ልዑል እግዚአብሔር ምሥጢሩን ለአገልጋዮቹ ነቢያት አስቀድሞ ሳይገልጽ ምንም ነገር አያደርግም፤"

የሚለውን መሠረት አድርገን በምናይበት ጊዜ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም የመጣው ሰላምና የኅሊና ዕረፍት አጥቶ ለተቸገረው ዓለም ወንጌልን አስተምሮ የልብ ሰላምንና የኅሊና ዕረፍትን ለማስጠት ሲሆን ለተራበው ዓለም ደግሞ የሕይወት እንጀራ ሊሆንና ደሆችም ሠርተው የሕይወት እንጀራን የሚያገኙበትን መንገድ በወንጌል አማካኝነት ለማስጠት ነው፡፡

ስለዚህ ተምሮ ማስተማር፣ አውቆ ማሳወቅ፣ አምላካዊ ትእዛዝ መሆኑን በማንዘብ አስተማሪ ሆኖ የሚያስተምር፣ ሐኪም ሆኖ የታመሙ ወገኖችን የሚያክም፣ አዋቂም ሆኖ በድንቁርና ጨለማ ውስጥ ያሉትን ወገኖቹን በሚችለው ሁሉ የሚረዳ ከሆነ ከታሪክና ከእግዚአብሔር ወቀሳ እንዲሁም ከተጠያቂነት የሚድን አይሆንም፡፡ በመሠረቱ ማህራን የእግዚአብሔርን ሕግ አስፈጻሚዎች

ናቸው፣ የማኅበራዊ ኑሮ ቅመሞች ናቸው፤ ከሥርዐትና ከሕግ ውጭ የሚመላለሱትን ወደ ሕግ ክልል አስገቢዎች ናቸው፡፡ እንደ ቃለ ወንጌሉ መምህራን የዓለም ጨው የዓለምም ብርሃን ናቸው "ሰዎች መልካም ሥራችሁን አይተው የሰማዩ አባታችሁን እንዲያመሰግኑት ብርሃናችሁ በሰው ፊት ይብራ፤" ተብለዋልና (ማቴ. 5÷16)፡፡ በዘመናችን ሰው ለራሱ፣ ሰው ለኑሮ ጓደኛው፣ ሰው ለልጆቹ፣ ሰው ለኅብረተሰቡ አልፎ ተርፎም ለእግዚአብሔርም ሕግ እንኳ ያልታመነበት ጊዜ ስለሆነ ይህን ከመስመር የወጣ ሰውን፣ ወደ ትክክለኛው መስመር እንዲገባ የሚደረግ ግዴታና ኃላፊነት የመምህራን መሆኑን ልንገነዘበው ይገባል፡፡ ያለበለዚያ "ለደከሙት እንክብካቤን አላደረጋችሁላቸውም፤ የታመሙትን አላዳናችሁም፤ የተሰበሩትን አልጠገናችሁም፤ የባዘኑትን አልመለሳችሁም የጠፉትን አልፈለጋችሁም፤" የሚለውን ትንቢታዊ ጥያቄ ማስከተሉ አይቀርም፤ (ሕዝ. 34÷4)፡፡

"በአደራ የተቀበላችሁትን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፡፡" (1ጴጥ. 5÷2-11)

ለቤተ ክርስቲያን ከተሰጡት የበረከት ስጦታዎች መካከል አንዱና ዋናው እረኝነት ነው ሥራውም በዝርዝር ሲገለጽ፡-

ሀ. አስተዳዳሪነት፣

ለ. መጋቢነት፣

ሐ. ጠባቂነት፣

ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ "መንፈስ ቅዱስ እናንተን የመንጋው ጠባቂ አድርጎ ሾሟችኋል፣ እንግዲህ ለራሳችሁና ለመንጋው ተጠንቀቁ፡፡ በልጁ ሞት የራሱ ያደረጋትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ጠብቁ፣ እኔ ከሄድኩ በኋላ ለመንጋው የማይራሩ እንደተኩላ ጨካኞች የሆኑ ሰዎች እንደሚገቡ አውቃለሁ"፡፡ (የሐዋ. ሥራ 20÷28) በማለት በሰፊው ያስገነዝባል፣ የእረኝነትም ተግባር ምን እንደሚመስል ሥዕላዊ መግለጫ ይሰጣል፡፡

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም "ስጦታዎችን ለሰዎች የሰጠ እርሱ ነው፤ ስለዚህ አንዳንዶቹ ሐዋርያት፣ አንዳንዶቹ ነቢያት፣ አንዳንዶቹ የወንጌል ሰባኪዎች፣ አንዳንዶቹ የምእመናን እረኞች፣ አንዳንዶቹ አስተማሪዎች እንዲሆኑ አድርጓል"፡፡ (ኤፌ. 4÷11) እያለ በስፋት የገለጸውን ልብ ማለት ያስፈልጋል፡፡

በቤተ ክርስቲያን የእረኝነት (የጠባቂነት) ሥራ ከተሰማሩት አንዱ ቅዱስ ጴጥሮስ እንደእርሱ የክርስቶስን መንጋ የማጠበቅና የመመገብ አደራ ለተቀበሉት እረኞች ሲጽፍ የሁሉም እረኛ ሊቀ ካህናት (ሊቀ ኖሎት) ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ የክብር አክሊልን ለመቀበል እንድትበቁ፡፡

- ረብ (ሥጋዊ ጥቅም) ለማግኘት ባለማቀድ፣
- በግድ ሳይሆን በፍቅር በማስተዳደር፣
- ምሳሌ በመሆን መንጋውን ጠብቁ እያለ በብርቱ ያሳስባል፡፡ (1ጴጥ. 5÷1-4)

በዘመነ ብሉይ ኪዳን እስራኤል ዘሥጋ የእግዚአብሔር መንጋ ነበር፡፡ (መዝ. 74÷1-2፣ 79÷13፣ 80÷1፣ 95÷7)

አሁንም በዘመነ ሐዲስ ኪዳን የእስራኤል ዘነፍስ የእግዚአብሔር መንጋ እረኛ ራሱ ባለቤቱ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑ ባይዘነጋም እንደ ቃሉ በተዋረድ ሐዋርያት፣ መምህራን በአጠቃላይም አዕይንተ እግዚአብሔር የተባልን ካህናት ሁላችን ነን፡፡ የተሰጠንን ኃላፊነት በአግባቡ እየተወጣን ነው? (ዮሐ. 10÷16፣ ዮሐ. 20÷28፣ ዮሐ. 21÷15-17)

## ለ. ልጆችን በጥበብ ማሳደግ

ምእመናን ከእርሱ በመንፈስ ስለተወለዱ "አባ አባት" ብለው ይጠሩታል (ማቴ.6÷9፣ ዮሐ.1÷12፣ 1÷13፣ ገላ. 4÷6)፡፡

አባትና እናት በግብር ስማቸው ወላጆች ይባላሉ፡፡ የወላጆች ዋና ሥራ ልጆቻቸውን በጥበብ ማሳደግ ነው፡፡ (ምሳ. 1÷8፣ 4÷10-15) ልጆቻቸው

በተገቢው ሥርዓት እንዲያድጉ ማጠበቅ አስፈላጊ ሲሆን በአግባቡ ማሰጽም ይገባቸዋል፡፡ አባት ለልጆች ሃይማኖትን ያስተምራል (138፣ ዘዳ. 4÷9፣ 6÷7፣ 6÷20-25)፡፡

እንደ መጥምቀ ማለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ከእናታቸው ማኅፀን ጀምሮ እግዚአብሔር የሚጣቸውና ለእግዚአብሔር የሚዘሁ ሕፃናት አሉ፡፡ ነቢዩ ዳዊት "ነፍሴን ከሞት፣ እግሮቼን ከመወደቅ አድነሃል" (መዝ. 55÷13) እንደአለው የሚጠበቅና የሚያድን እግዚአብሔር ቢሆንም ኅብረተሰብ የዐቅሙን ያህል ለሕፃናት እንክብካቤ ማድረግ አለበት፡፡

"ደግ ሰው እንደዘንባባ ያፈራል" (መዝ. 91÷12-13) እንዳለው ሚልካም አረኞች የሆኑት ካህናተ እግዚአብሔር ልጆቻቸው በመንፈሳዊ ጥበብ ካደጉ ለራስ፣ ለሀገርና ለሃይማኖት የሚጠቅም ዜጋን ያፈራሉ፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ አብርሃም ልጁን ይስሐቅን ጡት ባስጣለበት ቀን ታላቅ ግብዣ እንዳደረገ ይነግረናል (ዘፍ. 21÷8)፡፡ ከዚህ የምንረዳው የወላጆች ደስታ የልጆች መወለድ ብቻ ሳይሆን ማደጋቸውም እንደሆነ ነው፡፡ የአብርሃም ጥማት በእርሱ እግር ተተክቶ ቤቱን የሚያስተዳድር፣ ንብረቱን የሚወርስ ልጅ ማግኘት ነበር፡፡ ለዚህ ነው ይስሐቅን ጡት ባስጣለበት ቀን ታላቅ ግብዣ ያደረገው፡፡ ጡት የጣለ ልጅ እያደገ ለመሆኑ ማለጫ ነው፡፡ ያደገ ልጅ ለኃላፊነት ብቁ ነው፡፡ ስናድግ የተደረገልንን ለሌሎች ማድረግ እንጀምራለን፡፡ ወራሾች በመሆናችንም የሌሎችን ኃላፊነት እንሸከማለን፡፡ ጡት ያልጠበ ልጅ ግን አሁንም የሌሎች እንክብካቤን የሚፈልግና ከራሱ ወጪ ለሌላው የሚያስብ በመሆኑ የወላጆች ድካም ነው፡፡ ልጆችን ጡት ማስጣልም በጣም አድካሚ ሲሆን ልጆች ከጡት ጋር ታላቅ ፍቅር ስለሚኖራቸው ይህን ፍቅር ለመቁረጥ ልዩ ልዩ ዘዴዎችን ማጠቀም ግድ ይላል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ጡቱን መራራ ነገር በመቀባት ወይም ልጁ የሚጠላውን ነገር በማድረግ ልጁና ጡቱ እንዲቆራረጡ ይደረጋል፡፡

በእግዚአብሔር ተራዳኢነት ወጣቶችም በፈተና ምሬት ይህን ዓለም እንዲለቀቁትያስፈልጋል፡፡የእግዚአብሔርአገልጋዮች ካህናትም ልጆቻቸው በመንፈሳዊ

ጥበብ አድገው በተማከረለት ማንነት እንዲገልጡ ለቀጣዩም አገልግሎት ተረካቢ እንዲሆኑ ሙድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ "አህያ በወለደች ታርፋለች" ነውና፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "ልጅ ሳለሁ እንደ ልጅ እናገር ነበረ፣ እንደ ልጅም አስብ ነበር፣ ጐልማሳ ሆኜ ግን የልጅነትን ጠባይ ሽሬአለሁ" በማለት እንደቷት በእውቀት እንዳደገ መግለጹ እና ልጁ ጢሞቴዎስን "ሙጽግህ በነገር ሁሉ እንዲገለጥና ይህን አስብ" ማለቱ የወጣቶች ድርቅ ለማልሞ ለፍሬ እንዲበቃ ነው፡፡ (1ኛ ቆሮ.13÷11፣ 1ኛ ጢሞ. 4÷15)

በዓለማችን ለሰው ልጅ የሚጠቅመውን ሁሉ እየሠሩ የኖሩና የሚኖሩ ብዙ ደጋግ ሰዎች የመኖራቸውን ያህል፣ በአንፃሩም ለሰው ልጅ የሚበጀውንና የሚጠቅመውን እያደረጉ የሚኖሩም አይታጡም፡ ታዲያ ለደጋጎቹ ጻድቃን ቅዱሳን የሚል ስመ ተጸውዖ ሲሰጣቸው፣ ለሚልካም ሥራ ያልታደሉት ደግሞ በክፉ ሥራቸው ኃጥአን፣ እኩያን፣ የሚል ስያሜ እንደተሰጣቸው በቅዱስ መጽሐፍ እንረዳለን፤ (ማቴ. 25÷31-46)፡፡ ጠቢቡ ሰሎሞንም የእግዚአብሔርን ቃል በማስተማር ስለሚጽክሙ ደጋግ ሰዎች (ቅዱሳን) ሲገልጽ "የጻድቅ ሰው ከንፈሮች ብዙ ሰዎችን ይመግባሉ፤ ከፉዎች ግን ከልባቸው ጉድለት የተነሳ ይሞታሉ፡፡ (ምሳ. 10÷21)" በማለት የመዝገበው የደጋግ ሰዎችንና የከፉዎች ሰዎች ዝንባሌን በማብራራት የከተበው (የጻፈው) ነው፡፡

በዓለማችን ላይ ክፋትም ደግነትም የመኖሩን ያህል ደጉን ከክፋት፣ ጽድቁን ከኃጢአት ለይቶ መኖር የደጋግ ሰዎች ዓይነተኛ ማለያ ነው፡፡ ቅዱሳን የእግዚአብሔርን ቃል ለተራቡት በመመገብ፣ ክርስቲያናዊ መንገድ ጠፍቷቸው በጨለማ ሲጓዙ ለነበሩት የወንጌልን ብርሃን በማብራት፣ ሕይወት ወደሚገኝበት ሕገ ወንጌል እየመሩ ብዙዎችን አድነዋል፡፡ ስለዚህ ነው"ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊት ጻድቅ" ወይም ደግ ሰው እንደ ዘንባባ ያፈራል፤ በደጋ እንደተተከለ ዝግባ ይሆናል፡፡ ፍሬ በረከትንም ያፈራል ሲል የተናገረው፡፡

ቅዱሳን ነቢያት እነ ቅዱስ ኤርምያስ፣ እነ ቅዱስ ሕዝቅኤል፣ እነ ቅዱስ ዳንኤል፣ እነ ዕዝራ፣ እነ ጦቢት፣ እነ አቤሜሌክ ስለ ሀገራቸው ስለ

ኢየሩሳሌም መጥፋት፣ ስለ ወገኖቻቸው መማረክና ማሰደድ፣ ስለ ቤተ መቅደስ መፍረስ፣ ስለ ሕጋቸው መደምሰስ እያዘኑና እያለቀሱ ይጸልዩ እንደነበረ፣ ሁሉ ዛሬም በዓለም ላይ ሥር የሰደደውን የሰውን ልጆች ከገጸ ምድር ለመደምሰስ ግብ ላይ የሚገኘውን የግብረሰዶማዊነት አደጋ ከሕዝብ ጫንቃ ላይ አውርዶ ለመጣል ከላይ እንደተጠቀሱት ቅዱሳን ነቢያት ለሕዝብ ችግር የቆሙ ምሁራን ማስፈለጋቸው አጠያያቂ አይደለም፡፡ የወገን ችግር የማይሰማው ምሁር ካለ ምሁር አይደለም፡፡ ለሀገርና ለወገን የማያስብና የማይጨነቅ የማያዝንና የማያለቅስ፣ በጸሎትም የማይተጋ ካለ፣ ቁጥሩ ከደጋጎቹ ሳይሆን ከክፉዎቹ ሆኖ ሚፈረጅ የማይቀር ነው፡፡ ፈጣሪያችን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በደሙ ያገዘውን ዓለም የሚጠብቅ ሰው በነፍስ በሥጋ ይፈረድበታል፡፡

"ጥበብ ያለው ሁሉ ይህን ያስተውል፣ ልብ ያለውም ይህን ነገር ይወቅ የእግዚአብሔር መንገድ ቅን ነው፤ ጻድቃን ይሄዱበታል፣ ኃጢአተኞች ግን ይሰናከሉበታል"፡፡ (ሆሴ. 14÷8)

**ስብሐት ለእግዚአብሔር**

**ወለወላዲቱ ድንግል**

**ወለመስቀሉ ክቡር**

**አሜን**

**አነሳስቶ ለአስጀመረን አስጀምሮ ላስፈጸመን ለልዑል**

**እግዚአብሔር ምስጋና ይግባው፡፡**

**ስብሐት ለእግዚአብሔር አሜን!!**

**ብፁዕ አባታችን አቡነ ሳሙኤል**

**በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን**

**ልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን**

**ሊቀ ጳጳስ**

**አዲስ አበባ ኢትዮጵያ**

**፳፻፲ ዓ.ም**